# የሃሳብ ልዩነትንና ተቃዉሞን ማዳፈን

## በንግግር እና በጽሁፍ ነጻነት ላይ ያነጣጠረ የተፋፋመ ጥቃት በኢትዮጵያ

AMNESTY INTERNATIONAL

## የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እትመት

**በመጀመሪያ እ. አ. አ. 2011 ዓ. ም. ታተመ**
**Amnesty International Publications**
**International Secretariat**
**Peter Benenson House**
**1 Easton Street**
**London WC1X 0DW**
**United Kingdom**
**www.amnesty.org**

**© የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እትመት 2011**

**የመግለጫው መለያ፡ AFR 25/011/2011**
**ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተተረጎመ**
**በአምነስቲ ኢንተርናሽናል የታተመ፤ ኢንተርናሽናል ሴክሬታሪያት፣ዩናይትድ ኪንግደም**

**ሁሉም ያሳታሚው የባለቤትነት መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው። የዚህ ህትመት የቅጂ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በማናቸውም መንገድ ይህን እትመት በማባዛትያልክፍያ ግንዛቤ ለማስጨበጫነት፣ ለቅስቀሳ እና ለማስተማሪያ አገልግሎቶች እንዲውል መጠቀም የሚቻል ሲሆን በሽያጭ መልክ ማሰራጨት የተከለከለ ነው። ህትመቱ ከዝህ በላይ ለተጠቀሱት አላማዎች ከዋለ፣ የህትመቱን ጠቀሜታ መገምገም ይቻለው ዘንድ ተጠቃሚዎቹ እንዲያሳውቁት አሳታሚው ይጠይቃል። ከተጠቀሱት ውጭ በሌላ ማንኛውም ሁኔታዎች ወይም ለሌላ እትመት አገልግሎት ለመጠቀም ወይም ለመተርጎም ወይም ለማሳተም በቅድሚያ የአሳታሚው በጽሑፍ የተረጋገጠ ፈቃድ ያስፈልጋል፤ እንዲሁም ክፍያም ሊጠይቅበት ይችላል።**
**ፈቃድ ለመጠየቅ ወይም ለማንኛውም ተጨማሪ መረጃ የሚከተለ አድራሻ የጠቀሙ።**

**copyright@amnesty.org**

**አምነስቲ ኢንተርናሽናል አለም አቀፋዊ ንቅናቄ ሲሆን ከ3 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ደጋፊዎቹ፣ አባላቱ እና ተሳታፊዎቹ በ150 አገራት እና ግዛቶች ውስጥ አስከፊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ረገጣዎች እንዲቆሙ በመታገል ላይ ይገኛሉ።**

**አላማችን ለእያንዳንዱ ሰው በአለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ እና በሌሎች አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች የተጠበቁት መብቶች ሁሉ እንዲከበሩ ነው።**

**ከማንኛውም መንግስት፣ ፖለቲካዊ አመለካከት፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይም ኃይማኖት ገለልተኛ ስንሆን ገቢያችንን በዋናነት የምናሰባስበው ከአባላት መዋጮና ከገለልተኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሚገኙ እርዳታዎች ነው።**

AMNESTY
INTERNATIONAL

## ማውጫ


መቅድም ---------- 5

**ክፍል አንድ፡-** እሥራት እና የወንጀል ክሶች---------- **8**

እሥራት ---------- 8

በኦሮሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ የተፈጸመ እሥራት (ከመጋቢት/ ምያዚያ እና ከነሐሴ/መስከረም)---------- 8

ሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ገለልተኛ ጋዜጠኞች ላይ የተፈጸመ እሥራት (ከሰኔ - መስከረም) ---------- 10

የየቀረቡትወንጀል ክሶች---------- 10

በኦሮሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ የቀረቡ የወንጀል ክሶች ---------- 11

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በተሻለ በካሺ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ---------- 11

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በጌትነት ገመቹ ገመታ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ---------- 12

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በበቀለ ገርባ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ---------- 12

በሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች ላይ የቀረቡ የወንጀል ክሶች---------- 12

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በኤልያስ ክፍሌ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ---------- 12

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በአብዲወሊ ሞሀመድ ኢስማኤል እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ---------- 13

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በአንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ---------- 13

**ክፍል ሁለት፡-** የተለዩ አስተሳሰቦችን በሚያራምዱ ሰዎች ላይ ያነጣጠረ እርምጃ ---------- **15**

ስለ ታሳሪዎቹ ማንነት አጭር መግለጫ---------- 15

የኦሕኮ እና ኦፌዴን ታሳሪዎች ---------- 15

የሰኔ እና ሐምሌ ወር ታሳሪዎች ---------- 16

በመስከረም ወር የታሰሩትን በተመለከተ---------- 16

በሌሉበት ክስ የተመሰረተባቸው ---------- 18

ሃሳብን በነጻነት መግለጽ እንደ ማስረጃ ሆኖ ስለመቅረቡ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ---------- 19

ለሽብርተኝነት የተሰጠ ከልክ ያለፈ ሰፊ ትርጓሜ ---------- 21

እስራቶችቹን እና የፍርድ ሂደቶቹን አስመልክቶ በከፍተኛ ደረጃ የተንጸባረቁ የፖለቲካ ፍላጎቶች---------- 22

**ክፍል ሦስት፡-** ከፍርድ ሂደቱ መጀመር በፊት በእስር ቤት የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶች ---------- **24**

በእስር ላይ እንዳሉ በቤተሰቦቻቸው እንዳይጎበኙ መከልከል ---------- 24

ጠበቃ የማግኘት መብትን መነፈግ ---------- 25

ማሰቃየትና ሌሎች ዓይነት በደሎችን ማድረስ ---------- 26

ማሰቃየትና ሌሎች ዓይነት በደሎችን በመፈጸም የተገኙ ማስረጃዎች---------- 28

በማሰቃየትና ሌሎች ዓይነት በደሎችን በመፈጸም የተገኙ ማስረጃዎች ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ---------- 29

**ክፍል አራት፡-** የፍርድ ሂደቱን በተሟላ መልኩ የመከታተል አስፈላጊነት ---------- **30**

**ማጠቃለያ፡-** የቀጠለው የጥቃት ዘመቻ እና ሃሳብን በመግለጽ ነጻነት ላይ እያሳደረ ያለው ከፍተኛ ተጽእኖ ---------- 31

የመፍትሄ ሃሳቦች------------------------------------------------------------------------------------------------------- 32

**ተጨማሪ መግለጫ፡-** በስድስት ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ክሶች እና ተከሳሾች-------------------------------------------------------- 34

በተሻለ በካሺ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ ---------------------------------------------------------------------------- 34

በጌትነት ገመቹ ገመታ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ------------------------------------------------------------------ 36

በበቀለ ገርባ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ----------------------------------------------------------------------------- 36

በኤልያስ ክፍለ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ--------------------------------------------------------------------------- 36

በአብዲወሊ ሞሀመድ ኢስማኤል እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ--------------------------------------------------------- 37

በአንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ--------------------------------------------------------------------- 37

# መቅድም

ከመጋቢት 2011 ዓ.ም* ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ ወደ መቶ ስምንት (108) የሚጠጉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ስድስት ጋዜጠኞች በሽብርተኝነት ከተፈረጁ ቡድኖች ጋር ግንኙነት ፈጥራችኋል በሚል ተይዘው ለእስር ተዳርገዋል። እስከ ህዳር ወር ባለዉ ጊዜ ከታሳሪዎቹ መካከል በመቶ ሰባቱ (107) ላይ የጸረ-ሽብር አዋጁን እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን ተላልፋችኋል በሚል የወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል። ሌሎች ከአገሪቱ ውጭ በስደት ላይ በሚገኙ ስድስት ጋዜጠኞች፣ ሁለት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና አንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ላይም በሌሉበት ተመሳሳይ ክስ ተመስርቶባቸዋል። ይህ መግለጫ እየተጠናቀረ ባለበት ወቅት በተጠቀሱት ሁሉም ጉዳዮች የፍርድ ሂደት ተጀምሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እምነት በአገሪቷ ውስጥ እየታየ ያለው ተከታታይ እና የረጂም ጊዜ እስራትና እንዲሁም፣ ክሶች የሚያመላክቱት መንግሥት ሕግንና ጸረ-ሽብር ዘመቻን ሰበብ በማድረግ በመንግሥት ተግባራትና ፖሊሲዎች ላይ የሰሉ ትችቶችን የሚሰነዝሩትን እና ጥያቄዎችን የሚያነሱ ሰዎችን፤ በተለይም ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን እና ገለልተኛ የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን ለማፈን ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚጠቀም መሆኑን ነው። ምንም እንኳን እነዚህ ወገኖች ቀደም ሲል ለተደጋጋሚ ጊዜያት ታስረው ክስ የተመሰረተባቸው ቢሆንም እንዲዚህ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በአንድ ጊዜ ለእስር የመዳረጋቸው ሁኔታ የሚያመላክተው በአገሪቷ ውስጥ ሃሳብን በመግለጽ ነጻነት ላይ የሚደርሰዉ አፈና በ2011 እ.ኢ.አ የተባባሰ መሆኑንን ነው።

በ2011 ዓ.ም ለእስር ከተዳረጉት መካከል አብዛኛዎቹ የጋዜጠኝነት ሙያቸውን እና የተቃዋሚ ፖለቲከኝነት ድርሻቸውን ሕጋዊ መሠረት ባለው መልኩ ለመወጣት በአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ በሚሰጧቸው አስተያየቶች እና በመንግሥት ተግባራት ላይ በሚሰነዝሩዋቸው የሰሉ ትችቶች የሚታወቁ ነበሩ። በዚህም የተነሳ ቀደም ሲል ብዙዎቹ ለረዥም ጊዜያት በመንግስት ኃይሎች ማዋከብ ሲደርስባቸው፤ አንዳንዴም ለእስራትና ለወንጀል ክሶች ተዳርገዋል። ይህ በ2011 እ ኢ አ የታየው በርካቶችን የማሰር ተግባር የተከሰተው ግለሰቦች በገሃድ በመንግሥት ላይ የሰላ ትችት መሰንዘራቸዉን፣ የፖሊሲ ለውጦችን በሚጠይቁ ሕዝባዊ ጥሪዎች መሳተፋቸዉን፣ መንግሥት ከፍተኛ ተቃውሞ ሊቀሰቀስ ይችላል ብሎ በሰጋበት ወቅት ሰላማዊ ሰልፎችን ለማካሄድ የሚጠይቁ የፈቃድ ማመልከቻዎች መቅረባቸውን፤ ወይም መንግሥት እንዳይጎበኝ ጥብቅ እቀባ ባደረገበት የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ስላለው ሁኔታ የጋዜጠኝነት ምርመራ ለማካሄድ ሙከራ የተደረጉባቸውን ቀናቶች ተከትሎ ነው።

በተከሳሾቹ ላይ የቀረቡት እና በክስ መዝገቡም ላይ የተዘረዘሩት አብዛኛዎቹ ማስረጃዎች የሽብር ተግባርም ሆነ የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ሊያረጋግጡ የማይችሉ ነገሮችና ተግባራትን ያካትታሉ። ይልቁንም አብዛኛዎቹ በማስረጃነት የቀረቡት ነገሮች ግለሰቦቹ ሃሳብን የመግለጽ ነፃነታቸውን በአግባቡ መጠቀማቸውን፤ እንዲሁም በጋዜጠኝነታቸውም ሆነ በተቃዋሚ ፓርቲ አባልነታቸዉ ያከናወኑዋቸው ተግባራት ሰላማዊና ሕጋዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ እንጂ የወንጀል ቅጣትን ሊያስከትሉባቸው የሚችሉ አይደሉም። ከተጠቀሱት ማስረጃዎችም መካከል ተከላካዮቹ መንግስትን በመተቸት የጻፉዋቸው ጽሑፎች ወይም ጋዜጠኞች የዘገቡዋቸው የሰላማዊ ተቃውሞ ጥሪዎች ተካተውበታል። ከአንዳንዶቹ ክሶች ጋር በተያያዘም ከልክ ባለፈ መልኩ በሰፊው የተተረጎመው የጸረ-ሽብር ሕግ አዋጅ የተለየ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ግለሰቦችን ለመክሰስ በሥራ ላይ ውሏል። ሰላማዊ ተቃውሞዎችን ለማካሄድ የተደረጉ ሕዝባዊ ጥሪዎች በሽብር ተግባርነት ተፈርጀዋል።

*በዚህ መግለጫ የተጠቀሱት ቀናት በሙሉ የተመለከቱት እንደ አውሮፓዉያን አቆጣጠር ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአገሪቱ ፓርላማ ባቀረቡት ሪፖርት ሁሉም ተከሳሾች ወንጀለኞች ናቸው በማለት ለአገሪቱ ፓርላማ የሰጡትን የአቋም መግለጫ ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ባሳዩት የተለየ ፍላጎት እና በሰጡዋቸው መግለጫዎች ምክንያት የእነዚህ ግለሰቦች የክስ ሂደት በከፍተኛ ሁኔታ ፖለቲካዊ አቅጣጫን እንዲይዝ መደረጉን ያሳያል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል እነዚህ በመንግሥት ባለሥልጣናት የሚሰነዘሩት አስተያየቶች በፍርድ ቤቶቹ ላይ ፖለቲካዊ ጫናዎችን ሊያስከትሉ ይችላሉ የሚል ስጋት አለው። እንዲሁም እነዚህ አስተያየቶች ተከሳሾቹ ወንጀለኝነታቸው በፍርድ እስከሚረጋገጥ ድረስ ነጻ ሆነው የመገመት መብታቸውን የሚጥስ ነው።

በ2011 ዓ.ም ከታሰሩት መቶ አሥራ አራት (114) የሚሆኑት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች በቅደሚያ ማዕከላዊ ተብሎ በሚታወቀው እስር ቤት ውስጥ እንዲቆዩ የተደረገ ሲሆን በቆዩበትም ጊዜ በኢትዮጵያ እና በዓለም አቀፍ ሕጎች የተደነገጉትን ለእስረኞች የሚገቡ መብቶችን ተነፍገዋል። ሁሉም ታሳሪዎች ከተያዙበት ዕለት ጀምሮ የሕግ አማካሪዎችን እንዳያገኙና በቤተሰቦቻቸውም እንዳይጎበኙ በመከልከላቸው ታሳሪዎቹ ለሌሎች የሰበዓዊ መብቶች ጥሰቶች የመጋለጣቸውን ሁኔታ እጅግ ከፍ አድርጎታል። ከታሳሪዎቹ መካከል አብዛኞዎቹ ለፍርድ ቤት ጭምር ባሰሙት አቤቱታ በማዕከላዊ እስር ቤት ውስጥ በነበራቸው ቆይታ እና በምርመራውም ሂደት የማሰቃየት ድርጊትና ሌሎች በደሎችም ይደርሱባቸው እንደነበር ገልጸዋል፤ ያሉን እንደሚያመለክቱት ፍርድ ቤቱ የታሳሪዎቹን አቤቱታ ያደመጠ ቢሆንም የማሰቃየት ተግባር የተፈጸመባቸው ስለመሆኑ ያቀረቡትን አንዳቸውንም አቤቱታዎች ተጣርቶ እንዲቅርብ ተእዛዝ ያልሰጠ ሲሆን በመንግሥት ባለሥልጣናት በኩልም ጉዳዩን ለማጣራት ምንም አይነት ፍላጎት አላሳዩም። አብዛኞዎቹ ታሳሪዎች ጥፋተኛ ነኝ በሚል በተዘጋጀ የእምነት ቃል ማረጋገጫ ሰነድ ላይ ፊርማቸውን እንዲያኖሩ መገደዳቸውን፤ አለያም እነሱን ለመወንጀያ በማስረጃነት የተሰበሰቡትን ቁሳቁችና ሰነዶችን የእነሱ ንብረቶች መሆናቸውን ወይም ከተጠቀሱት ማስረጃዎች ጋር አንድ ዓይነት ግንኙነት ያላቸው መሆኑን እንዲያምኑ ስለመገደዳቸው ተዘግቧል።

እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እምነት በዚህ መግለጫ የተካተቱት ሁሉም ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በዋነኝነት ለእስር የተዳረጉት ሕግን መሠረት በማድረግና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መንግሥት ላይ ትችቶችን በመሰንዘራቸው ሲሆን በጉዳዩ ላይ የታየው ከፍ ያለ የፖለቲካ አትኩሮት የፍርድ ሂደቱ ገለልተኛነት ሊዛባ የሚችልበትን ሁኔታ ከፍ ያደርገዋል። በሰፊው ሲዘገብ እንደቆየው ከፍርዱ ሂደቱ መጀመር በፊት በእስር ቆይታቸው ወቅት የተፈጸሙባቸው የሰብዓዊ መብቶች እረገጣ፤ እና ይሄው ጉዳይ በፍርድ ሂደቱ ወቅት በተደጋጋሚ ጊዜያት በአቤቱታ መልክ ቀርቦ ምንም ውጤት ሳያገኝ መቅረቱ እነዚህ ወገኖች ገለልተኛ የሆነ ዳኝነት አያገኙም ብቻ ሳይሆን ሳይሆን ታሳሪዎቹ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ እና የመደራጀት መብታቸውን በአግባቡ በመጠቀማቸው ብቻ ሊፈረድባቸው ይችላል የሚል ስጋት ። በመሆኑም በዚህ መግለጫ ውስጥ የተጠቀሱትን ስድስቱን የክስ ሂደቶች ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ባለው የነጻ ዳኝነት ሂደት መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት በተሟላ ሁኔታ በቅርብመከታተል አስፈላጊ ሆኗል። የፍርድ ሂደቶችን ለመከታተል የሚችሉ የሲቪክ ማህበራት በሌሉበት ሁኔታ፤ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በአዲስ አበባ የሚገኙ የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ተወካዮች የፍርድ ሂደቱን የመከታተል ኃላፊነቱን እንዲወስዱ ጥሪውን ያቀርባል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመንግሥት በኩል ተጨማሪ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትን የማሰር ሃሳብ እንዳለመግለጻቸው አፈናው ገና እንዳላበቃ የሚያመላክት ሲሆን እስሩም ቀጥሏል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል በደረሰው መረጃ መሰረት በታኅሳስ ወር የመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ ቢያንስ 135 የሚጠጉ ሰዎች በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ታስረዋል። ከመካከላቸውም የኦሮሞ ሕዝቦች ኮንግረስ እና የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቀ አባላትና ደጋፊዎች ይገኙበታል።

እነዚህ እስሮች፣ የወንጀል ክሶች እና ገና በቀጣይነት የሚስተዋለዉ የመንግሥት ከፍ ያለ የፖለቲካ ፍላጎትና ጣልቃ ገብነት በኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ሰፊ የሆነ እንድምታ አለቸው። የተጠቀሱት ተግባራት ለፖለቲካ ተቃዋሚዎች፣ ጋዜጠኞች እንዲሁም መንግሥት የሚከተላቸው ፖሊሲዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች ያሳስበኛል ለሚል

ለማንኛውም ሰው የሚያስተላልፉት የማስጠንቃቂያ መልዕክት ቢኖር ከመናገርና ምንም ጥያቄዎችን ከማንሳት እንዲታቀቡ፤ አለበልዚያ ግን የሚጠብቃቸው እስራት መሆኑን ነው። ይህንኑ በመስጋትም አንዳንድ ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፓርት አባላት አገር ለቀው ለመሰደድ ተገደዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በአገሪቱ ውስጥ የቀረችውን ጭላንጭል ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ሙሉ በሙሉ ለማዳፈን ቆርጦ የተነሳ ይመስላል። ከዕለት ወደ ዕለትም የተለየ አስተሳሰብን የሚያራምዱ ግለሰቦችና ህትመቶች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚወክሉ ሰዎች፤ እንዲሁም ባለው የፖለቲካ ሂደት ላይ ገለልተኛ የሆነ ትችቶችን ለመሰንዘር የሚሞክሩ ሰዎች ምንም ቦታ እንዳይኖራቸው እየተደረገ መጥቷል።

# ክፍል አንድ፡- እስራቶችና የወንጀል ክሶች

# እስራቶች

በ2011 ዓ.ም በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች ያላሳለሰ ጥቃት ደርሷልቀ። ቢያንስ ቁጥራቸው ወደ 114 የሚጠጉ ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላት፤ ታዋቂ አባላቶቻቸዉን ጨምሮ፤ ከመጋቢት እስከ መስከረም ወር ባሉት ጊዜያት ውስጥ ለእስር ተዳርገዋል። ከታሳሪዎቹም መካከል 98 የሁለቱ ዋነኛ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ሲሆኑ የታሰሩትም በመላው የኦሮሚያ ክልል እና አዲስ አበባ ውስጥ ነው። ከቀሩት ታሳሪዎ መካከል 10 የሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲ አባላቶችና 6 ነጻ ጋዜጠኞች የሚገኙ ሲሆን አብዛኛዎቹ አዲስ አበባ ውስጥ ነው የታሰሩት።

## የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርት አባላት እስር፡- ከመጋቢት እስከ ሚያዚያ እና ከነሐሴ እስከ መስከረም

በመጋቢት እና ሚያዝያ ወራት በኦሮሚያ ክልልና በአዲስ አበባ ውስጥ መንግስት ባካሄደው መጠነ ሰፊ ዘመቻ ቁጥራቸው 200 እስከ 300 የሚጠጉ የኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆች ታፍሰው ለእስር ተዳርገዋል።[1] ሞያሌን፣ ጅማን፣ ሐረርን እና ነቀምትን ጨምሮ በመላው ክልል እስራቶች ተዘግበዋል።

ከእነዚህ ታሳሪዎች መካከል 89 የሚሆኑት የሁለቱ አንጋፋ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ የኦሮሞ ሕዝቦች ኮንግረስ (ኦሕኮ) እና የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቀ (ኦፌዲን) አባላት ናቸው። አብዛኛዎቹ ታሳሪዎች ቀደም ሲል ከ2005 እስከ 2010 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) የክልላዊ ምክር ቤት ወይም የኦሮሚያ ክልል ጉባዔ አባላት የነበሩ እና በቀጣዩ የ2010 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) ለዳግም ጠቅላላ ምርጫ ወቅት ለመመረጥ ሳይሳካላቸው የቀሩ ናቸው። ለምሳሌ ያህል በሚያዚያ ወር ተይዘው የታሰሩት ብርሃኑ እምሩ የኦፌዲን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፊዚክስ መምህር ናቸው። ብርሃኑ በ2010 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) በተካሄደው መርጫ ላይ ለድርጅታቸው የምርጫ ቅስቀሳ ያካሂዱ የነበረና የፓርቲያቸውን መግለጫዎችና በመገናኛ ብዙሃን የሚሰራጩ ጽሑፎችን ያዘጋጁ ነበር። ሌሎች 32 ታሳሪዎች እነ አስፋው ነጋሶ፣ ጉቱ ሙለሳ እና መንገሻ ቶለሳን ጨምሮ በ2010 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) በተካሄደው መርጫ ላይ የኦሕኮ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ነበሩ። አስፋው ነጋሶ እና ጉቱ ሙለሳ ከ2005 እስከ 2010 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) የኦሕኮ የፓርላማ ተወካዮች ነበሩ።

የሁለቱ ፓርቲዎች አባላት የሆኑ በርካታ ተማሪዎች እና ወጣቶች፤ የ17 ዓመቷን የኦፌዲን ደጋፊ የነበረችን ወጣት ጨምሮ፤ በመጋቢትና ሚያዝያ ወር በጅምላ ከታሰሩት መካከል ይገኙበታል።

በሁለተኛው ዙር የጅምላ እስር ቁጥራቸው ቢያንስ 20 የሚሆኑ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ከነሐሴ ወር መጨረሻ እስከ መስከረም ወር መግቢያ ድርስ ባሉት ሳምንታት ውስጥ ለእስር ተዳርገዋል። ከእነዚህም ውስጥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህርና የኦፌዲን ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት በቀለ ገርባ እና የኦሕኮ ፓርቲ ባለሥልጣን የሆኑት አልባና

---

[1] መንግሥት የታሳሪዎቹን ቁጥር በተመለከተ፣ ምን ያህሎቹ ላይ ክስ እንደተመሠረት ወይም ምን ያህሎቹ ክስ ሳይመሰረትባቸው ከእስር እንደተፈቱ የሚገልጹ መረጃዎችን ይፋ ለማድረግ አልቻለም። ሁለቱ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተጎጂ ስለሆኑት አባላቶቻቸው ካሰባሰቡት መረጃ በስተቅር ይህን እስር በተመለከተ በአግባቡ ተጠናቅሮ የቀረበ መረጃ የለም።

ለሊሳን ጨምሮ ዘጠኝ የኦፌዲን እና የኦሕኮ አባላት ከታሳሪዎቹ መካከል ይገኙበታል። በቀለ ገርባ እና አልባና ለሊሳ ከመታሰራቸው ጥቂት ቀናት በፊት ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ተወካዮች ጋር በአካል ተገናኝተው ውይይት አድርገዋል።

ሁሉም በእስር ላይ የሚገኙት የኦፌዲን እና የኦሕኮ አባላት የታሰሩት የኦሮሞ ነፃ-አውጪ ግንባር (ኦነግ) አባላት ናቸው በሚል ጥርጣሬ ነው። ኦነግ የትጥቅ ትግልን የሚያካሂድ ቡድን ሲሆን በሰኔ ወር 2011 ዓ.ም (እ.ኢ.አ) በኢትዮጵያ ፓርላማ ሽብርተኛ ተብሎ የተፈረጀ ድርጅት ነው። ከዚህ ቀደም የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት የኦነግ አባላት ናችሁ በሚል በበርካታ ጊዜያት የወንጀል ክሶች ተመስርቶባቸዋል።

በመጋቢትና ሚያዝያ ወር በጅምላ ከታሰሩት በርካታ አባላቶቻቸው መካከል የተወሰኑት የደረሱብት እንደማይታወቅ ኦፌዲን እና ኦሕኮ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል የገልጹ ሲሆን ይህም  ግለሰቦች በሕገ-ወጥ እስር ላይ ይገኛሉ የሚል ስጋት ፈጥሯል። ታሳሪዎቹ ፍርድ ቤት ቀርበው እንደማያውቁ እና አሁንም በየት ሥፍራ እንደሚገኙ ማወቅ ያለመቻላቸውን ቤተሰቦቻቸዉ ለኦፌዲን እና ኦሕኮ ገልጸዋል  ፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በመጋቢትና ሚያዝያ ወር በኦሮሚያ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ታስረው ክስ ያልተመሰረተባቸውን ሰዎች ስምና ታስረው የሚገኙበትን ሥፍራ ጨምሮ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት ለመንግስት ጥያቄ አቅርቧል. ከመንግስት የተሰጠው ምላሽ ግን የትጠናቀረ መረጃ ስለሌለ የተጠየቀዉን አይነት ዝርዝር መስጠት አንችልም የሚል ነው።[2]

እንደ ኦሕኮ አመራር አካላት ገለጻ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተለይም በወለጋ፣ አምቦ እና በሐረር የኦሮሚያ አካባቢዎች ሰዎችን የማሰሩ ሂደት በመስከረም እና ህዳር ወር ውስጥም ቀጥሏል። በመስከረም ወር ውስጥ በቀለ አርጋሳ የተባል የአዳማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ታስሮ አዲስ አበባ ወደሚገኘው ማዕከላዊ እስር ቤት ተዛውሮ ክስ ሳይመሰረትበት በእስር ላይ ይገኛል። አርጋሳ በ2010 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) ምርጫ ኦሕኮን በመወከል ለኦሮሚያ ክልላዊ ምክር ቤት እጩ ተወዳዳሪ ነበር። መንግሥት ከምንግዜውም በከፋ መልኩ በማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች እና የመረጃ ልውውጦች ላይ ባሳደረው ጥብቅ ቁጥጥር የተነሳ የኦሕኮ አመራር አካላት ምን ያህል አባላቶቻቸው ለእስር እንደተዳረጉና ስለቀረቡባቸውም የክስ ዓይነቶች ዝርዝር መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተቸግረዋል።

በ2011 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) ሌሎች መንግሥት ላይ ትችት የሚሰነዝሩ ቡድኖችን የሚወክሉ ግለሰቦችም ለእስር ተዳርገዋል። በተለይም ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ተማሪዎች የጅማ፣ ሃሮማያ እና ነቀምት ዩኒቨርስቲዎችን ጨምሮ ከመላው የኦሮሚያ ክልል ተይዘው ለእስር ተዳርገዋል። የመንግሥት ባለሥልጣናት ይህን እስር በማስመልከት የታሳሪዎቹን ማንነት፣ በምን ጉዳይ ክስ እንደተመሰረተባቸው እና የት ሥፍራ እንደታሰሩም ሆነ ሌሎች መረጃዎችን ይፋ ከማድረግ ተቆጥበዋል። በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄደውን መጠነ ሰፊ እስራቶች እና ታሳሪዎች የሚገኙበትን ሁኔታ መከታተልና ማስረጃዎችን ማሰባሰብ የሚችሉ ሁነኛ የሲቪክ ማህበራት ብሌሉበት ሁኔታ፤[3] እነዚህ ጉዳዮች በበቂ ያልተዘገቡ ሲሆን በገለተኛ አካልም ክትተል እና ማጣራት አልተደረገባቸዉም። የታሳሪ ተማሪዎቹ ጉዳይ በዚህ መግለጫ ርእስ ስር  ያልተካተተ ቢሆንም የታሳሪዎቹ ጉዳይ ምን እንደደረሰ በቅርብ መከታተል ያስፈልጋል።

[2] በአምነስቲ ኢንተርናሽናልና በፍትሕ ሚኒስትር መካከል በነሐሴ ወር 2011 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) በተካሄደ ውይይት።

[3] በ2009 ዓ.ም. (እ.አ.አ) በሥራ ላይ የዋለው አፋኝ ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የሰበአዊ መብቶች ድርጅቶች በሙሉ አቅማቸው እንዳይንቀሳቀሱ ጠንካራ ገደብ ጥሎባቸዋል። በዚህ ሕግ መጽደቅ ሳቢያና በዳግም ምዝገባው ሂደት የገጠሟቸውን በርካታ መሰናክሎች ለመቋቋም የቻሉት የሰበዓዊ መብቶች ድርጅቶች በ2011 ዓ.ም. (እ.አ.አ) ከፍ ያለ የአቅም መዳከምና የበጀት እጥረት ተጋርጦባቸዋል።

## የሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ገለልተኛ ጋዜጠኞች እስር (ከሰኔ እስከ መስከረም ወር)

ሰኔ 19 ቀን 2011 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) በየሳምንቱ እየታተመ የሚወጣው የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ የሆነው ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተይዞ ታስሯል። ከሁለት ቀናት በኋላ በሰኔ 21 ደግሞ ርእዮት አለሙ የተባለችው የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህርት እና የፍትሕ ጋዜጣ ቋሚ አምደኛ ለተመሳሳይ እስር ተዳርጋለች። በዚሁ ሳምንት ውስጥ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች የሆኑት የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ፕሬዚደንት ዘርይሁን ገብረእግዚያብሔር እና የፓሪቲው አባል የሆኑት ደጀኔ ተፈራ ለእስር ተዳርገዋል። ሁሉም የታሰሩት በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው ነው።

ከዚያም ጥቂት ቆይቶ ሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) ማርቲን ሺበይ እና ዮሃን ፐርሶን የተባሉ ሁለት ሲውዲናዊ ጋዜጠኞች በሶማሌ ክልል ውስጥ ሲንቀሳቀሱ ተይዘው ታስረዋል። ጋዜጠኞቹ የተያዙትም ከኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነአግ) አባላት ጋር ነው ተብሏል።

በመስከረም ወር ደግሞ ታዋቂ የሆኑ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች እና ጋዜጠኞች ታስረዋል። መስከረም 8 ቀን በብዙዎች ዘንድ ታዋቂ የሆኑት የኪነ-ጥበብ ሰው እና የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ መስራች አባል፤ እንዲሁም በ2005 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) በተካሄደው ምርጫ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፖርቲ መስራች አባል የሆኑት ደበበ እሸቱ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተይዘው ታስረዋል። በቀጣዩ ቀንም መስከረም 9 ቀን አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኘዉ የኤፍ.ኤም 96.3 ሬዲዮ ጋዜጠኛ ስለሺ ሀጎስ ተይዘው ታስረዋል።

ከአምስት ቀናት በኋላ ታዋቂው ጋዜጠኛ እስክር ነጋ እና ተቃዋሚ ፖለቲከኛ የሆኑት አንዱዓለም አራጌ፣ ናትናዔል መኮንን፣ አሳምነው ብርሃኑ እና ዘመን ሞላ በአዲስ አበባ ውስጥ ተይዘው ለእስር ተዳርገዋል። አንዱዓለም አራጌ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር ናቸው። ናትናዔል መኮንን እና አሳምነው ብርሃኑ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት ናቸው። ዘመን ሞላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ዋና ጸሐፊ ናቸው።[4] አምስቱም ሰዎች የታሰሩት በመንግሥት ከታገደው የግንቦት 7 ንቅናቄ ለፍትሕ፣ ለነፃነት እና ዴሞክራሲ (ግንቦት 7) ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ጥርጣሬ ነው።

ክንፈሚካኤል ደበበ የተባሉት የተቃዋሚው የመላው ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ አባል መስከረም 26 ቀን ተይዘው ታስረዋል። እንደ ፓርቲው ባለሥልጣናት ገለጻ ከሆን ቢያንስ አንድ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ አባል፤ ገዛኸኝ (የአባት ስማቸው ያልታወቀ) በመስከረም ወር ውስጥ ለእስር ተዳርገዋል።

# የቀረቡት የወንጀል ክሶች

በ2011 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) የታሰሩት መቶ ሰባት (107) የሚሆኑት ጋዜጠኞች እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላቶች እስከ ህዳር ወር ክስ ተመስርቶባቸዋል። የቀሩትና በስደት ላይ የሚገኙት ስድስት ጋዜጠኞች፣ ሁለት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና አንድ የሰበዓዊ መብቶች ተሟጋች በሌሉበት ክስ ተመስርቶባቸዋል። በጥቅሉ መቶ አሥራ ስድስት ሰዎች ላይ በሕገ-ወጥነት ከተፈረጁ የሽብር

[4] በሰኔ ወር የታሰሩት ዘሪሁን ገብረእግዚያብሔር እና ደጀኔ ተፈራም የዚሁ ፓርቲ አባላት ናቸው።

ድርጅቶች[5] ጋር በማበርና የሽብር ተግባራትን ለመፈጸም በማቀድ ወንጀል ተጠርጥረዋል በሚል ክስ ተመስርቶባቸዋል። ክሶቹም በጸረ-ሽብር አዋጁ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ወስጥ የተደነገጉ ልዩ ልዩ የወንጀል ተግባራትን አካተዋል።[6]

ስለሺ ሐጎስ የተባለው ጋዜጠኛ እና አምስት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ አሳምነው ብርሃኑ፣ ዘመነ ሞላ፣ ደበበ እሸቱ፣ ደጀኔ ተፈራ እና ገዛሃኝ ፣ ክስ ሳይመሰረትባቸው ከእስር ተለቀዋል።

ቀሪዎቹ ታሳሪዎች በስድስት የተለያዩ መዝገቦች ክስ ተመስርቶባቸዋል። ከነዚህም ሦስቱ በኦሕኮን እና ኦፌዲን ፖለቲካ ፓርቲ አባላት ላይ የቀረቡ ናቸው። የተቀሩት ሦስት የክስ መዝገቦች በጋዜጠኞቹና በሌሎቹ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላቶች ላይ እንዲከላከሉ የቀረቡ ናቸው። በመጨረሻዎቹ ሦስት መዝገቦች ጋዜጠኞቹና ሌሎቹ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላቶች ከሌሎች ተከሳሽ ግለሰቦች ጋር ተጣምረው ነው የተከሰሱት። ምንም እንኳን የተከሰሱት በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት ተሳትፈዋል በሚል ቢሆንም፤ ከጣምራ ተከሳሾቹ መካከል አንዳንዶቹን ወይንም ሁሉንም ጨርሶ እንደየማያዉቋቸው በአጠቃላይ በስድስቱም መዝገቦች ክስ የቀረበባቸው ተከሳሾች አመልክተዋል።

# በኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ላይ የቀረቡ ክሶች

ዘጠና ስምንት (98) በሚሆኑት የኦፌዲን እና የኦሕኮ ፓርቲዎች አባላት ላይ የቀረበው ክስ ታሳሪዎቹ በኢትዮጵያ ፓርላማ የአሸባሪ ድርጅት ተብሎ ከተፈረጀው የኦሮሞ ነፃአውጪ ግንባር ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ነው። ይሁንና የተመሰረተባቸው ክስ የጸረ-ሽብር አዋጁን መሰረት በማድረግ ሳይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ዉስጥ በተደነገጉ የወንጀል አይነቶች ነው።

ዘጠና ስምንቱ ተከሳሾች በሦስት መዝገቦች ነው ክስ የተመሰረተባቸው። በመጋቢት እና ሚያዚያ ወር የታሰሩት ስልሣ ስምንቱ ተከሳሾች የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በተሻለ በካሺ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ በከፈተው የክስ መዝገብ ተካተዋል። እንዲሁ በመጋቢት እና ሚያዚያ ወር የታሰሩት የተቀሩት ሃያ (20) ተከሳሾች የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በጌትነት ገመቹ ገመታ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ በከፈተው የክስ መዝገብ ውስጥ ተካተዋል። በነሐሴ እና መስከረም ወር የታሰሩት ዘጠኝ (9) ተከሳሾች ደግሞ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በበቀለ ገርባ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ በከፈተው የክስ መዝገብ የተካተቱ ናቸው። በእነዚህ መዝገቦች ውስጥ ክስ የተመሰረተባቸው ግለሰቦች ስም ዝርዝር በዚህ መግለጫ አባሪ ውስጥ ይገኛል።

## የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በተሻለ በካሺ እና ሌሎች ላይ ያቀረበው ክስ

ስልሣ ዘጠኙ (69)[7] ተከሳሾች በተሻለ በካሺ እና ሌሎች የክስ መዝገብ ላይ ግንቦት 8 ቀን 2011 ዓ.ም. (እ.አ.አ) የቀረበባቸው ክስ፤

- 1ኛ ክስ፡- በሁሉም ተከሳሾች ላይ፤ "የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል" (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 241)

[5] በሰኔ ወር 2011 ዓ.ም. (እ.አ.አ) አምስት ድርጅቶች በኢትዮጵያ ፓርላማ የሽብር ድርጅቶች ተብለው ተፈርጀዋል። እነሱም የኦሮሞ ነፃአውጪ ግንባር እና የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር፤ ሁለቱም ታጣቂ ቡድኖች ለረዥም ጊዜ መጠነኛ የሆኑ ጥቃቶችን በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ሲሰነዝሩ የቆዩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በውጭ አገር የተቋቋመው የተቃዋሚ ቡድን የግንቦት 7 ለዴሞክራሲና ለፍትህ ንቅናቄ፣ አል-ሻባብ (በሱማሊያ የሚገኝ እስላማዊ ታጣቂ ቡድን) እና አል-ቃይዳ ናቸው።

[6] በ2005 ዓ.ም. (እ.አ.አ) ተሻሽሎ የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ።

[7] በሦስቱ ክሶች ውስጥ የተካተቱትን ተከሳሾች የስም ዝርዝር በአባሪ መግለጫው ላይ ይመልከቱ

- 2ኛ ክስ፦ በ2ኛ፣ 14ኛ፣ 40ኛ እና 61ኛ ተከሳሾች፤ “የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆን ዓይነት ማሰናዳት” (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 256)
- 3ኛ ክስ፦ በ8ኛ፣ 10ኛ፣ 14ኛ፣ 36ኛ፣ 57ኛ እና 63ኛ ተከሳሾች፤ “መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር” (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 257)[8]

### የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በጌትነት ገመቹ ገመታ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው የክስ

በሃያዎቹ ተከሳሾች ላይ በጌትነት ገመቹ ገመታ እና ሌሎች የክስ መዝገብ በሰኔ ወር ውስጥ የቀረበባቸው ክስ፤

- 1ኛ ክስ፦ በሁሉም ተከሳሾች ላይ፤ “የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል” (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 241)

### የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በበቀለ ገርባ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ

በዘጠኙ ተከሳሾች ላይ በፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በበቀለ ገርባ እና ሌሎች መዝገብ ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም. (እ.አ.አ) የከፈተው ክስ፤

- 1ኛ ክስ፦ በሁሉም ተከሳሾች ላይ፤ “የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል” (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 241)
- 2ኛ ክስ፦ በ9ኛ ተከሳሽ፤ “የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆን ዓይነት ማሰናዳት” (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 256)
- 3ኛ ክስ፦ በ2ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች፤ “መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር” (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 257[9])

## በሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ላይ የቀረቡ ክሶች

### የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በኤልያስ ክፍሌ እና ሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ

ጋዜጠኞች ውብሸት ታዬ እና እርዮት አለሙን ጨምሮ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ የሆኑት ዘርይሁን ገብረእግዚያብሄር ሂሩት ክፍሌ የተባሉ ሌላ ግለሰብ መስከረም 5 ቀን 2011 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ)በሽብር ወንጀል በጣምራ ተከሰዋል። ጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌም በሌለበት በዚህ ክስ ውስጥ ተካቷል። የተመሰረተባቸውም ክስ ከዚህ እንደሚከተለው የጸረ-ሽብር አዋጁን እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው።

---

[8] ይህ ክስ ‘ሕገ ማንግሥቱን ወይም መንግስትን በመጻረር የተፈጸመ ወንጀል” በሚል ረዕስ ከተከፈቱት ክሶች ጋር የሚዛመድና በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሁለተኛ ታላቅ ክፍል ሦስተኛ መጽሐፍ ‘በመንግሥት፣ በአገርና በዓለም አቀፍ ጥቅሞች ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች’ ውስጥ ‘በሕገ መንግሥቱ እና በመንግሥት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች’ በሚለው ንዑስ ክፍል ይካተታል።

[9] ከላይ እንደተገለጸው

- 1ኛ ክስ፦ በሁሉም ተከሳሾች ላይ፤ "ማንኛውንም የሕዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆነ" (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (6 እና/ወይም 4)፣ እና/ወይም የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም ማቀድ መዘጋጀት፣ማሴር ማነሳሳትና ሙከራ (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 4)፤
- 2ኛ ክስ፦ በሁሉም ተከሳሾች ላይ፤ "በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ" (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 7)፤
- 3ኛ ክስ፦ በሁሉም ተከሳሾች ላይ፤ "በሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘን ንብረት ስለመያዝና መገልገል" (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 9)፤
- 4ኛ ክስ፦ በሁሉም ተከሳች ላይ፤ "በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ መርዳት" (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 684)፤
- 5ኛ ክስ፦ በ1ኛ ተከሳሽ (ኤልያስ ክፍሌ) ላይ፤ "ለሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት" - የገንዘብ ወይም የፋይናንስ ወይም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶችን ለሽብር ተግባር ወይም ለአሸባሪ ቡድኖች በማቅረብ ወይም በመስጠ (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1/መ )

## የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በአብዲወሊ እና ሌሎች ተከሳሾች መዝገብ ያቀረበው ክስ

ኤልያስ ክፍሌ እና ሌሎች ተከሳሾች ከላይ በተጠቀሰው መዝገብ በተከሰሱበት ዕለት መስከረም 5 ቀን ስዊዲናዊዎቹ ጋዜጠኞች ማርቲን ካርል ሺቢ እና ጆሃን ከርል ፐርሰን በጸረ-ሽብር አዋጁ መሠረት የሽብር ተግባርን በመፈጸም እና በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በመግባታቸው በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት ክስ ተመስርቶባቸዋል። ከሺቢ እና ፐርሰን ጋር ሁለት የኦብነግ አባላት በጣምራ ተከሰዋል። እነዚህ አብዲወሊ ሙሃመድ ሂስማኤል እና ካሊፍ አሊ ዳሂር የተባሉት ሁለቱ የኦብነግ አባላት ከሁለቱ ስዊዲናዊ ጋዜጠኞች ጋር አብረው የተያዙ ሲሆን የጥፋተኝነት ውሳኔም በፍርድ ቤት ተሰጥቶባቸዋል።[10] ከዚህ በታች የሚከተለው የክስ ዝርዝር ሁለቱ ጋዜጠኞችን ብቻ የሚመለከት ነው።

- 1ኛ ክስ፦ በሁለቱም ተከሳሾች ላይ፤ "ለሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት" - በሙያ፣ በልምድ፣ በሞራል ምክር ወይም ድጋፍ በመስጠት (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ)፤
- 2ኛ ክስ፦ በሁለቱም ተከሳሾች ላይ፤ "በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ" (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 7). ይህ ክስ ህዳር 3 ቀን 2011 ዓ.ም. በዳኛ ውሳኔ ውድቅ ተደርጓል፤
- 3ኛ ክስ፦ በሁለቱም ተከሳሾች ላይ፡ 'የአገሪቱን የግዛት ወይም የፖለቲካ ሉአላዊነት በመጣስ፤ ለሕዝብ ደኅንነት አስጊ የሆነ ተግባር ለመፈጸም ወደ አገሪቱ ግዛት በመግባት፣ ወይም የኢትዮጵያ ሥልጣን በሆነው ተግባር ውስጥ በተለይም የምርመራ፣ የብርበራ ወይም የፍርድ አሠራር በሆነው ሥራ ውስጥ ገብቶ ለውጭ አገር መንግሥት ወይም ድርጅት ሲሰራ የተገኘ' (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 242)

## የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በአንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች ተከሳሾች መዝገብ ያቀረበው ክስ

ህዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም. (እ.አ.አ) እስክንድር ነጋ፣ አንዱዓለም አራጌ፣ ናትናኤል መኮንን፣ ክንፈሚካኤል ደበበ፣ ዮሐንስ ተረፈ፣ የሺዋስ ይሁንዓለም፣ ምትኩ ዳምጤ እና አንዱዓለም አያሌው ገላው የተለያዩ የወንጀል ተግባራትን ፈጽመዋል በሚል በጸረ-ሽብር አዋጁንና በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡ ሌሎች 16 (አሥራ ስድስት) ተከሳሾች በሌሉበት የተከሰሱ

[10] ሁለቱ በኦብነግ አባልነት የተጠረጠሩት ግለሰቦች ምንም አይነት መከላከያ ሳያቀርቡ እና ወዲያውኑ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥረው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል። በህዳር ወር መጀመሪያዉቹ ላይም እያንዳንዳቸው የ17 ዓምት እስር ተፈርዶባቸዋል።

ሲሆን ከመካከላቸው አምስቱን ጋዜጠኞች (ፋሲል የኔዓለም፣ አበበ በለው፣ አበበ ገላው፣ መስፍን ነጋሽ እና አቢይ ተክለማሪያም)፣ አንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች (አባንግ ሜቶ - የአኙዋክ የፍትህ ጉባዔ የተሰኘው የሰበዓዊ መብት ድርጅት ሊቀመንበር)፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪ የሆኑት ዘለሌ ጸጋሥላሴ፣ እንዲሁም ከሀገር ውጪ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አስተባባሪና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አስተዳዳሪ (ነአምን ዘለቀ) ይገኙበታል።[11]

ሃያ አራቱ (24) ተከሳሾች በጸረ-ሽብር አዋጁና በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተለያዩ አንቀጾች መሠረት እንደሚከተለው ተከሰዋል፡-

- 1ኛ ክስ፡- በሁሉም ተከሳሾች ላይ፡- "የሽብርተኝነት ድርጊቶች" በሚከተለው አኳኋን 'ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረስ እንደሆን፤ የኅብረተሰቡን ወይም የኅብረተሰቡን ክፍል ደህንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ እንደሆን፤ እገታ ወይም ጠለፋ የፈፀመ እንደሆን፤ በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆን፤ ማናቸውንም የህዝብ አገልግሎቶች ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆን' (የጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 3 ነዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 3፣ 4 እና 6)፤
- 2ኛ ክስ፡- በሁሉም ተከሳሾች ላይ፡- "የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም ማቀድ፣ መዘጋጀት፣ ማሴር፣ ማነሳሳትና ሙከራ" (የጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 4)፤
- 3ኛ ክስ፡- በሁሉም ተከሳሾች ላይ፡- "ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት" (የጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 6)፤
- 4ኛ ክስ፡- በሁሉም ተከሳሾች ላይ፡- "ከፍ ያለ ክዳት" በሚከተለው አኳኋን 'ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ከሚያደርግ ኃይል ጋር ወይም ለዚሁ ኃይል ጥቅም ከሚሠራ ሰው ወይም ድርጅት ጋር በመተባበር ወይም ምስጢር ግንኙነት ማድረግ' (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 248) (ማስታወሻ፡- ከእዚህ ክስ ጋር በተያያዘ በክሱ ላይ በጠላትነት የተጠቀሰው የኤርትራ መንግሥት ነው)
- 5ኛ ክስ፡- በሁሉም ተከሳሾች ላይ፡- "ስለላ" (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 252 (1/ሀ) )፤
- 6ኛ ክስ፡- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 18 ስማቸው በተጠቀሰው ተከሳሾች ላይ (አባሪውን ይመልከቱ)፡- "በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ" በሚከተለው አኳኋን 'ማንኛውንም ሰው በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ በአመራርነት ወይም በውሳኔ ሰጪነት የሰራ እንደሆን' (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 7/2 )፤
- 7ኛ ክስ፡- በ19ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች (ኤልያስ ሞላ እና ደሳለኝ አራጌ ዋሌ) ላይ፡- "በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ" በሚከተለው አኳኋን 'ማንኛውንም ሰው ለሽብርተኛ ድርጅት ወይም የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ለመፈጸም ሰው የመለመል ወይም አባል የሆነ ወይም ስልጠና የወሰደ ወይም በድርጅቱ በማናቸውም መልክ የተሳተፈ እንደሆነ' (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 7/1 )፤
- 8ኛ ክስ፡- በ23ኛ እና 24ኛ ተከሳሾች (መስፍን ነጋሽ እና አቢይ ተክለማሪያም) ላይ፡- "ለሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት" (ጸረ-ሽብር አዋጅ አንቀጽ 5)፤

በህዳር ወር መጨረሻ አካባቢ ዓቃቤ ሕጉ ለፍርድ ቤት ባቀረበው ሪፖርት መስፍን ነጋሽ እና አቢይ ተክለማሪያም (23ኛ እና 24ኛ ተከሳሾች) በመጀመሪያው ክስ ያልተከሰሱ መሆኑንና ስማቸውም የተካተተው በጽሑፍ ስህተት መሆኑን ገልጿል።

[11] በክስ መዝገቡ ላይ የተጠቀሱትን ተከሳሾች ሙሉ የስም ዝርዝር በአባሪ መግለጫው መመልከት ይቻላል

# ክፍል ሁለት፡- በሃሳብ ልዩነትና ተቃውሞ ላይ ያነጣጠረ እርምጃ

## ስለ ታሳሪዎቹ ማንነት አጭር መግለጫ

በ2011 ዓ.ም. ከታሳሪዎቹ መካከል አብዛኛዎቹ እንደ ጋዜጠኝነታቸውና ተቃዋሚ ፖለቲከኝነታቸው ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በመንግሥት ፖሊሲዎችና ተግባራት ላይ በሚሰነዝሩት ሂስ እና ከመታሰራቸው በፊትም ባሉት ጥቂት ቀናቶች ውስጥ ባደረጉት የለውጥ ጥሪ የሚታወቁ ናቸው። አብዛኛዎቹም ላለፉት በርካታ ዓመታት በመንግስት ማዋከብ፣ እስራትና ክስ ደርሶባቸዋል።

ባብዛኛው የእስር እርምጃዎቹ የተወሰዱት ግለሰቦቹ ለውጥ የሚጠይቁ ጥሪዎችን በይፋ ማስተላለፋቸውን ተከትሎ፣ ወይም መንግሥት ታላቅ ተቃውሞ ሊገጥመኝ ይችላል ብሎ በሰጋባቸው ወቅቶች ሰላማዊ ሰልፎችን ለማካሄድ የፈቃድ ከጠየቁ በኋላ፣ እንዲሁም ሁለቱን ስዊዲናዊ ጋዜጠኞች በተመለከተ፣ መንግሥት እንዳይነበኝ ጥብቅ ክልከላ ካደረገበት የኢትዮጵያ ክልል ዘገባ ለማቅረብ ሲሞክሩ ነው።

በአምነስቲ ኢንተርናሽናል እምነት በዚህ መግለጫ ውስጥ የተካተቱት ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የታሰሩትም ሆነ በወንጀል የተከሰሱት ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መልኩ ባከናውኗቸው የጋዜጠኝነትና የፖለቲከኛነት ተግባራት ብቻ ነው።

## የኦሕኮ እና ኦፌዴን ታሳሪዎች

አነግን መደገፍ የሚለው ውንጀላ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማፈን በተደጋጋሚ ጊዜያት በጥቅም ላይ ውሏል። ለመቁጠር በሚያዳግት ሁኔታ በርካታ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት በዚህ መንገድ ለእስራት እና የወንጀል ክሶች ተዳርገዋል። ለምሳሌ ያህል በየካቲት ወር 2010 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) ለዋናው ምርጫ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት ኦሕኮ በሰጠው መግለጫ አምስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከ150 (ከመቶ ሃምሳ) በላይ የሚሆኑ የፓርቲው አመራር አካላት ለአነግ ድጋፍ ያደርጋሉ በሚል መታሰራቸውን ገልጿል።

በ2011 ዓ.ም. ለእስር የተዳረጉት በርካታዎቹ የኦሕኮ እና የኦፌዴን ፓርቲዎች አባላት ለ የፖለቲካ እንቅስቃሰዎችን ሲያደርጉ፤ በተለይም ለ2010 ዓ.ም. ምርጫ ቅስቀሳዎች በሚካሄዱበት ወቅት ለረዥም ግዜ ወከባና እንግልት ደርሶባቸዋልበመጋቢት እና ሚያዚያ ወራት ውስጥ ከታሰሩት የሁለቱ ፓርቲዎች አባላት መካከል አንዳንዶቹ ከመታሰራቸው አንድ ሳምንት በፊት ባሉ ቀናቶች ውስጥ የገኘውን ፓርቲ የማይቀላቀሉ ከሆነ እስር እንደሚገጥማቸው የሚገልጽ የስልክ ማስጠንቀቂያዎች ይደርሷቸው እንደነበር ገልጸዋል።

በነሐሴ ወር ውስጥ ለእስር የተዳረጉት በቀለ ገርባ እና አልባና ሌሊሳ ተደጋጋሚ የሆነ ማዋከብ እርምጃ የደረሰባቸው ሲሆን በተለይም በ2010 ዓ.ም. የምርጫ ዘመቻ ወቅት ወከባው የከፋ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። ከመታሰራቸውም ቀደም ብለው ባሉት ቀናት በጸጥታ ሃይሎች ክትትል ይደረግባቸው የነበረ ሲሆን በዚሁ ወቅት በቀለ ገርባ ከሚገናኛቸው ሰዎች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ተጠይቋል። በቀለ ገርባ እና አልባና ከመታሰራቸው ጥቂት ቀናችት በፊትም ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ተወካዮች ጋር

በአካል ተገናኝተው ነበር። በዚህም ወቅት የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ተወካዮች አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሚገኘው የበቀለ ገርባ ቢሮ በመውጣት ላይ እንዳሉ የሲቪል ልብስ በለበሱ የደኅንነት አባላት ፎቶ ግራፍ ተነስተዋል። የደኅንነት አባላቱ ፎቶ ግራፉን ለማንሳት ከቢሮው ደጃፍ ላይ ቆመው ተወካዮቹ እስከሚወጡ ይጠባበቁ ነበር።

# የሰኔ እና ሐምሌ ወር ታሳሪዎች

ርእዮት አለሙ ከመታሰሯ ጥቂት ቀናቶች በፊት ፍትሕ በሚባለው ጋዜጣ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን የሚተች ጽሑፍ ጽፋ ነበር። በተጨማሪም ከዩ.ኤስ.ኤ ለሚሰራጨውና መንግሥትን ላይ ጠንካራ ነቀፌታን በመሰንዘር ለሚታወቀው የኢትዮጵያን ሪቪው ድኅረ ገጽ ጽሑፍ ታበረክት ነበር። ለፖለቲካ ፓርቲው በሚያደርገው እንቅስቃሴአ የተነሳ ዘሪሁን ገብረእግዚያብሔር እጅግ በርካታ የሆኑ የመንግስትን ፖሊሲዎችን እና እርምጃዎችን የሚተቹ መግለጫዎችን ያዘጋጅ ነበር። ከመታሰሩ በፊት አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዘሪሁን ገብረእግዚያብሔር ግንቦት 28 (እ.ኢ.አ) በማእከላዊ አዲስ አበባ ሊካሄድ ለታሰበ ሰልፍ ፍቃድ ጠይቆ ነበር። ሆኖም በተጠቀሰው ቀንና ቦታ ላይ መንግሥትን የሚደግፍ ሰልፍ ለማካሄድና ገዥው ፓርቲም ወደ ስልጣን የመጣበትን 20ኛ ዓመት ክብረ በዓል በስፍራው ስለሚያከብር በሚል ምክንያት ፍቃድ ተከልክሏል።

ሲውዲናውያኑጋዜጠኞች ማርቲን ሺቢ እና ጆሃን ፐርሰን የታሰሩት ሐምሌ 1 ቀን በሱማሌ ክልል ውስጥ ነበር። በክልሉ ወስጥ የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻአውጪ ግንባር ላለፉት 18 ዓመታት ሽምቅ ውጊያ ሲያካሂድ ቆይቷል። ይህ ቡድን በሰኔ ወር 2011 ዓ.ም. አሸባሪ ድርጅት ተብሎ በኢትዮጵያ ፓርላማ ተፈርጇል።[12] በክልሉ ወስጥ የኢትዮጵያ መንግስት ወታደሮችና አጋር የሆኑ የአካባቢው ታጣቂ ሚሊሻዎች በንጹሃን ዜጎች ላይ ከፍተኛ የሰበዓዊ መብቶች ጥሰት እንደሚፈጽሙ ከክልሉ በተከታታይ የሚወጡ ዘገባዎች። መንግስት ጋዜጠኞች፣ የሰበአዊ መብቶችን የሚከታተሉ ወገኖች እና ሌሎች አጣሪ አካላት ስፍራውን እንዳይጎበኙ ጥብቅ እገዳ ያደርጋል። ቀደም ሲልም በርካታ የውጭ ጋዜጠኞችም ወድ ክልሉ በመጓዝ ሁኔታውን ሊዘግቡ ሲሉ ተይዘው ከታሰሩ በኋላ ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ ተደርገዋል።[13] ሺቢ እና ፐርስንም ክልሉ ውስጥ ዘልቀው በመግባት ያለውን ሁኔታ ለመዘገብ የሞከሩት በህቡእ ከኦብነግ ጋር ሆነው ነበር። ጋዜጠኞቹ እንደገለጹት ይከታተሉ የነበረው ሲውዲንን በክልሉ ውስጥ ከሚካሄደው አወዛጋቢ ከሆነው የነዳጅ ፍለጋ ጋር የሚያገናኙ ዘገባዎችን መነሻ በማድረግ ነው።

# በመስከረም ወር የታሰሩትን በተመለከተ

እስክንድር ነጋ እና አንዱዓለም አራጌ የታሰሩት መስከረም 12 (እ.ኢ.አ)ከዋለው ከኢትዮጵያ አዲስ ዓመት በኋላ ብዙም ሳይቆይ ነው። ሁለቱም በአዲስ አመት መልዕክታቸው የለውጥ ጥሪ አስተላልፈው ነበር። እስክንድር ነጋ በኢትዮጵያ ስላለው የፕሬስ ነፃነት ማብራሪያ ያደረገ ሲሆን በሕትመት ይፋ ባደረገውም ጽሑፍም 'ምናልባት 2004 ዓ.ም. (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) ሃሳብን የመግለጽና የመደራጀት ነፃነት የሚከበሩበት ዓመት፣ .... ምናልባት 2004 ዓ.ም. ኢትዮጵያዊያን በፖለቲካ እምነታቸው የተነሳ ለእስር የማይዳረጉበት ዓመት ሊሆን ይችላል' ብሎሎ ነበር። ይህን ካል ከአምስት ቀናት በኋላ ለእስር ተዳርጓል።

አንዱዓለም አራጌ በመንግስት ፖሊሲና ተግባራት ላይ ተከታታይ ሂሶችን በሚሰነዝረው በአንድነት ፓርቲ ጋዜጣ ህትመት በቅርብ ይሳተፍ ነበር። አንዱዓለም በ2004 የአንድነት ፓርቲን የአዲስ ዓመት መለዕክት በገለጸበት ወቅት '2004 ... የሕጋዊና ሰላማዊ

---

[12] ሽብርተኛ ቡድን ተብሎ መፈረጁ ከላይ ከተገለጸው ከኦሮሞ ነጻአውጪ ግንባር ጋር ባንድ ላይ

[13] በ2010 ዓ.ም. ለአሜሪካን ድምጽ የሚሰራ ጋዜጠኛ ክልሉ ውስጥ ስላለው የእርስ በእርስ ግጭት ከሐረር ከተማ ሆኑ በመዘገቡ የተነሳ ከኢትዮጵያ ተገዶ እንዲወጣ ተደርጓል። በ2007 ዓ.ም. ሌሎች ሦስት የኒዮርክ ታይምስ ጋዜጠኞች በሶማሊያ ክልል ውስጥ ያለውን ሁኔታ ለመዘገብ እንደተገለጸው ከሆነ በኦብነግ ተደግፈው ሲንቀሳቀሱ ተይዘው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ተደርገዋል።

ትግል ዓመት ይሆናል ... ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሁሉን ዓቀፍ የሆነ ነፃነትን ያጎናጽፋል’ ነበር ያለው። ይህን ከተናገረ ጥቂት ቀናቶችን በኋላ ለእስር ተዳርጓል።

ዘመነ ሞላም ከመታሰሩ ትንሽ ቀደም ብሎ ከተለያዩ አነስተኛ ተቃዋሚ ፖርቲዎች ጋር በመሆን ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄ የፍቃድ ማመልከቻ አቅርቦ ነበር። ከአዲስ አበባ መስተዳድር መልስ በመጠባበቅ እና ከባለሥልጣናቱ ለጥቄያቸው ምላሽ ምላሽ መነፈጋቸውን አስመልክቶም በቀጣዩ ቀን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ መስከረም 14 ቀን (እ.ኢ.አ) ተይዞ ታስሯል።

ስለሺ ሃጎስ መቀመጫው አዲስ አበባ ለሆነው የኤፍ.ኤም 96.3 የራዲዮ ስርጭት በጋዜጠኝነት የሚያገለግልና ቀደም ሲልም ‘ለውጥ’ የተባለው በሰኔ ወር 2011 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ፓርላማ የሽብርተኛ ቡድን ተብሎ ከመፈረጁ በፊት የግንቦት 7 ንቅናቄ ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የእንቅስቃሴዎች ይዘግብ የነበረው ወርሃዊ የፖለቲካ ምጽሔት አስተዳዳሪ ነበር። ስለሺ ሃጎስ በሰኔ ወር የታሰረችው የጋዜጠኛ ርእዮት አለሙ ጉዋደኛም ነው። ርእዮት በማዕከላዊ እስር ቤት በታሰረችበት ወቅትም ስለሺ በተደጋጋሚ ጊዜያት እየተመላለሰ ጎብኝቷታል። እርዮት ከታሰረች ከአጭር ጊዜ በኋላ በሐምሌ ወር ውስጥም ባለሥጣናት ስለሺን በማስጠራት ከርእዮት ጋር ስላለው ግንኙነት ምርመራ ካደረጉበት በኋላ ላፐቶፑን ነጥቀውታል።

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ቀደም ሲል ለማዋከብ፣ ለእስራት እና ለክሶች ተዳርጓል። አሁን የቀረበበትን የሽብር ወንጀል ክስ ጨምሮ እስክንድር የጋዜጠኝነት ሥራውን በማከናወኑ ምክንያት ብቻ ለስምንተኛ ጊዜ እስራትና ክስ ደርሶበታል። ቀደም ሲል “በቅንጅት የፍርድ ሂደት”[14] እስክንድር ነጋ፣ አንዱዓለም አራጌ እና ደበበ እሸቱ የእስክንድር ነጋ ባለቤት ከሆነችው ሰርካለም ፋሲል እና ሌሎች 127 (መቶ ሃያ ሰባት) ተቃዋሚ ፖለቲኮኞች፣ ጋዜጠኞችና የሲቪክ ማኅበረሰቡ አባላት ጋር በ2005 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ ከተቀሰቀሰው ተቃውሞ ጋር በተያያዘ በአገር ክህደትና በሌሎች ወንጀሎች ተከሰው ጉዳያቸው ከ 2005 እስከ 2007 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ)ባለው ጊዜ ሲታይቆይቷል።[15] ሁሉም ጥፋተኞች ተብለው ከተፈረደባቸው በኋላ በፕሬዝዳንቱ ምህረት ከእስር ተፈተዋል። ሆኖም እስክንድር፣ አንዱዓለምና ደበበ እሸቱ በ2007 ዓ.ም. ከእስር ከተለቀቁበት ጊዜ አንስቶ ከፍተኛ በሆነ የደኅንነት ኃይሎች ክትትል ስር ነበሩ።

የሺዋስ ይሁንዓለም ቀደም ሲል የአንድነት ፓርቲ አባል የነበረ እና በ2010 ዓ.ም. ምርጫ የጎጃም አካባቢ እጩ ተወዳዳሪ ነበር። በምርጫው ወቅት በፓርቲው እንቅስቃሰዎች ላይ በነበረው ንቁ ተሳትፎ የተነሳም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ከፍተኛ የሆነ ማዋከብ በተደጋጋሚ ጊዜ ደርሶበታል። አንድነት ፓርቲ የሺዋስ ይሁንዓለም አባል ሆኖ መቀጠሉን ማረጋገጥ አልቻለም። አንዱዓለም አያሌው ገላው የ ከ2005 እስከ 2010 ዓ.ም. ድረስ የቅንጅት ፓርቲ[16] የፓርላማ አባል የነበረ ሲሆን በ2010 ዓ.ም. በተካሄደው ምርጫ የአንድነት ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ ነበርች ይሁንና ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ ከፖሊስ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ይጠቀማቸው ስለነበሩ ገለጻዎች ማብራሪያ እንዲሰጥ የሚያስፈራራ ደብዳቤ እንደደረሰው ወደ ሱዳን ለመሰደድ ተገዷል። በሱዳንም የጥገኝነት ፈቃድ አግኝቶ ነበር። ሆኖም በህዳር ወር እንደታወቀው ካርቱም ከተማ በሚገኙ የኢትዮጵያ መንግስት የደኅንነት ኃይሎች ታፍኖ በግዳጅ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ተደርጓል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል በደረሰው መረጃ መሰረት በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ የሱዳን የጸጥታ ኃይሎች በአፈናው ላይ ተሳታፊ ሆነዋል። በክሱ እንደተገለጸውም አያሌው ከጥቅምት 25 ቀን (እ.ኢ.አ) ጀምሮ በአዲስ አበባ ማዕከላዊ እስር ቤት ታስሮ ቆይቷል።

---

[14] “የቅንጅት ፍርድ ሂደት” ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት ከተከሳሾቹ መካከል አብላጫዎቹ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አባላት ስለሆኑ ወይም ሁሉም ከቅንጅት ጋር ግንኙነት አላቸው ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው።

[15] በእዚህ የፍርድ ሂደት ውስጥ ከተካተቱት 131 ተከሳሾች መካከል ፋሲል የኔዓለም እና ብርሃኑ ነጋ (በፍርዱ ሂደት ወስጥ የተገኙ) እና ኤልያስ ክፍሌ እና አንዳርጋቸው ጽጌ (በሌሉበት የተከሰሱ)፤ እንዲሁም አራቱም ከላይ በተገለጸው “በአንዱዓለም እስክንድር” የክስ መዝጋብ ውስጥ በሌሉበት የተከሰሱ ናቸው።

[16] በቅንጅት ውስት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ተወካይ ነበሩ።

# በሌሉበት ክስ የተመሰረተባቸው

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኃይለማሪያም ደሳለኝ በሚመሩት የሚኒስቲር መስሪያ ቤት ሥር ለሚገኘው የሕግ ክፍል ከኢትዮጵያ ውጭ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ እና በካናዳ በሚኖሩና መንግስት በመቃወም በሚታወቁ ግለሰቦች ላይ ማስረጃ እንዲዘጋጅ መጠየቃቸውን የመገናኛ ብዙሃን በመጋቢት ወር ውስጥ ዘግበዋል ።

ርእዮት ዓለሙና ሌሎች ተከሳሾች ጋር በሌለበት ክስ የተመሰረተበት ኤልያስ ክፍሌ በመንግስት ፖሊሲዎችና ተግባራት ላይ፤ እንዲሁም በተወሰኑ የገዥው ፓርቲ አባላት ላይ ከፍተኛ የሆነ ትችቶችን በመሰንዘር የሚታወቀው 'የኢትዮጵያን ሪቪው' ድህረ ገጽ አዘጋጅ ነው።

ከአንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች ተከሳሾች ጋር በጣምራ በሌሉበት የተከሰሱት 16 ግለሰቦች፤ አምስት ጋዜጠኞችን፣ አንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሚጋች፣ በመንግስት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪን እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥምረት አስተባባሪና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አስተዳዳሪ የሆኑትን ግለሰብ ያካትታል።

በሌሉበት ክስ ከተመሰረተባቸው መካከል ሁለቱ ጋዜጠኞች፤ መስፍን ነጋሽ እና አብይ ተክለማርያም ታዋቂነትን ያተረፈው ነጻ ጋዜጣ የአዲስ ነገር አዘጋጆች ናቸው። በ2009 ዓ.ም. (እ.አ.አ) በመንግስት ባለሥልጣናት ተደጋጋሚ የሆነ ወከባና ማስፈራሪያ ሲደርስባቸው ከቆየ በኋላ የአዲስ ነገር ጋዜጣ አሳታሚዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የጋዜጣውን ህትመት ለማቆም የተገደዱ ሲሆን ነጋሽና ተክለማርያምን ጨምሮ የተወሰኑት ነባር ሠራተኞች አገር ለቀው ተሰደዋል። ጋዜጠኞቹ ከአገር ከተሰደዱ በኋላም የአዲስ ነገርን ድኅረ ገጽ በመክፈት በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡትን አስተያየቶች ቀጥለዋል።

የተቀሩት በሌሉበት ክስ የተመሰረተባቸው ጋዜጠኞች፤ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ጋዜጠኛ ፋሲል የኔዓለም፣ የአዲስ ቮይስ ራዲዮ ጋዜጠኛና የኢሳት ቴሌቪዥን የቦርድ አባል አበበ ገላው እና የአዲስ ድምጽ ራዲዮ ጋዜጠኛና የኢሳት ቦርድም አባል የሆነው አበበ በለው ናቸው።

የአዲስ ነገር እና የኢትዮጵያን ሪቪው ድኅረ ገጾች ኢትዮጵያ እንዳይታዩ በመንግስት ተዘግተዋል. የአዲስ ቮይስና አዲስ ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያዎችም እንደዚሁ ። የኢሳት ቴሌቪዥን ስርጭቱን ወደ ኢትዮጵያ የሚያስተላልፈው በሳተላይት ነው። ይሁንና እንደ ድርጅቱ ገለጻ ስርጭቱ ባለፈው ዓመት ውስጥ ብቻ ለሰባት ጊዜያት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይተላለፍ በመታገዱ የተነሳ ጣቢያው ለበርካታ ጊዜያት የተለያዩ የስርጭት መስመሮችን ለመቀያየር ተገዷል።

የአኝዋክ ፍትህ ጉባዔ ሊቀመንበር የሆኑት ኦባንግ ሜቶም በሌለበት በህዳር ወር ውስጥ ክስ ከተመሰረተባቸው ሰዎች አንዱ ነው። የአኝዋክ ፍትሕ ጉባዔ መንግስታዊ ያልሆነና ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኝ ድርጅት ሲሆን በደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያ በጋምቤላ ክልል ውስጥ በሚኖሩት የአኝዋክ ተወላጆች ላይ ስለሚፈጸመው የመብት ረገጣ ጥናቶችን የሚያካሂድና የሚከራከር ድርጅት ነው። በቅርቡ የአኝዋክ ፍትሕ ጉባዔ ካከናወናቸው ተግባራት መካከል አንዱ በአሁኑ ሰዓት በጋምቤላ ክልል ውስጥ ስለሚካሄደው ይፈጸማል ስለሚባለው የመሬት ቅርምት ጉዳይ ጥናቶችንና የገንዘቤ ማስጨበጫ ስራዎችን አካሂዷል። የመሬት ቅርምቱ ሂደትም እጅግ ሰፊ የሆኑ የእርሻ መሬቶችን ለውጭ ኩባንያዎች በሊዝ ኪራይ አሳልፎ በመስጠት በመሬቱ ላይ ይኖሩ የነበሩትን የአካባቢውን ነዋሪዎች ብዙውን ጊዜ በኃይል አስገድዶ ወደ ሌላ ቦታ ማስፈርን ያካተተ ነው። ሌሎች በሌሉበት የተከሰሱት የመላው ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ መሪና የነበሩት እና ከ2010 ዓ.ም. ምርጫ በኋላ ከአገር የተሰደደው ዘለሌ

ጸጋሥላሴ ፤ እንዲሁም ከአገር ውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አስተባባሪ እንደሆነ የተገለጸው ነዓምን ዘለቀ ይገኙበታል።

ከተቀሩት ስምንቱ በሌሉበት ክስ የተመሰረተባቸው ሰዎች መካከል አራት የግንቦት 7 አባላት የሆኑት አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ብርሃኑ ነጋ፣ ኤፍሬም ማዴቦ እና መስፍን አማን ሲሆኑ፣ አንድ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ አባል (በኮ/ል አለበል አማረ የሚመራ በውጭ የሚገኝና በትጥቅ ትግል የተሰማራ የተቃዋሚ ንቅናቄ)፣ እና ሦስት የፖለቲካ አቋዋማቸው ያልታወቀ ግለሰቦች (ደሳለኝ አራጌ ዋለ፣ ውቤ ሮቤ እና ኤልያስ ሞላ) ይገኙበታል።

በሌሉበት ክስ ከተመሰረተባቸ ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ ከእዚህ ቀደም ታስረውና ተከሰው የሚያውቁ ናቸው። ፋሲል የኔዓለም እና ብርሃኑ ነጋ ሁለቱም ከእስክንድር ነጋ እና አንዱዓለም አራጌ ጋር ከ2005 – 2007 ዓ.ም. በነበርው የቅንጅት ፍርድ ሂደት ውስጥ በአገር ክዳትና ሌሎች ወንጀሎች ተከሰው ነበር።[17] ኤልያስ ክፍሌ እና አንዳርጋቸው ጽጌም በሌሉበት በቅንጅት የፍርድ ሂደት ውስጥ ተከሰው ነበር። ሁሉም የትፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው ሲሆን በፕሬዚደንቱ ምህረት ነፃ ወጥተዋል። ፋሲል የኔዓለም እና ብርሃኑ ነጋ ከእስር ከተለቀቁ በኋላ አገር ለቀው ተሰደዋል። በኋላም ብርሃኑ ነጋ የግንቦት 7 ንቅናቄ ለፍትሕና ለዴሞክራሲን መሰረቱ።

# ሃሳብን በነጻነት መግለጽ እንደ ማስረጃ ሆኖ ስለመቅረቡ የሚያሳዩ ምሳሌዎች

በስድስቱ የክስ መዝገቦች ውስጥ በተከሳሾቹ ላይ በማስረጃነት የተዘረዘሩት ነገሮች ግለሰቦቹ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽና የመደራጀት መብታቸውን ለመጠቀማቸው ምሳሌ ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉ ተግባራትን ይጨምራሉ። ይህ መንግስትን በሰላማዊ መንገድ መቃወም እንደ ሕገ-ወጥ ተግባር የሚተረጎም መሆኑን ያመላክታል። የተጠቀሱት የማስረጃ አይነቶች ተከሳሾቹ ያንጸባርቋቸውን የተለዩ የፖለቲካ አስተሳሰቦች፣ መንግስት ላይ የሰነዘሩዋቸው ነቀፌታዎች፣ ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ የጋዜጠኝነት እና ሕጋዊ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባል በመሆን ያከናወኑዋቸው ተግባራት ያካትታሉ።

ከክስ መዝገቡ ጋር ተያይዞ በቀረበው የማስረጃ ዝርዝር ውስጥ በጋዜጦችና በድኅረ ገጾች ላይ የታተሙ መንግስትን የሚተቹ ጽሑፎች፣ መንግስትን በመንቀፍ በሚታወቁ የዜና ማሰራጫዎች የተገለጹ ነገሮች፣ የፖለቲካ ለውጥ እንዲካሄድ ጥሪ የሚያስተላልፉ ግጥሞች፣ በመካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ ስለተካሄዱት ሕዝባዊ ንቅናቄዎች የተጻፉ ጽሑፎች እና ለውጥን በተመለከተ የተዘጋጁ ውይይት መድረኮችን የሚመለከቱ ይገኙበታል።

በርእዮት አለሙ፣ ውብእሸት ታዮ፣ ዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር እና ኤልያስ ክፍሌ ላይ ከቀረቡት 51 (ሃምሳ አንድ) የማስረጃ አይነቶች መካከል 21 (ሃያ አንድ) የሚሆኑት ኤልያስ ክፍሌ ከሚያስተዳድረው 'ኢትዮጵያን ሪቪው ድኅረ-ገጽ የተወሰዱ ናቸው። በማስረጃ ዝርዝሩ ውስጥ ካሉት በርካታ የተቀነጣጠቡ ማስረጃዎች የሚገልጹት በቃ! በሚል መፈክር በአዲስ አበባ ከተማ ስለተሰራጩ መግለጫዎችና ፎቶግራፎች ነው። የበቃ! እንቅስቃሴ ገዥው ፓርቲ ወደ ሥልጣን የመጣበትን 20ኛ ክብረ በዓል በሚያከብርበት ዕለት ግንቦት 28 ቀን (እ.ኢ.አ) መንግስትን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፎች እንዲካሄዱ ጥሪ አስተላልፎ ነበር። በቃ! የሚለው መፈክር በከተማዋ የተለያዩ ስፍራዎች በየግርግዳው ላይ ብግራፊቲ መልክ እና በበራሪ ወረቀቶችም ላይ ታትሞ በህቡዕ

[17] ከላይ ይመልከቱ

መሰራጨት ጀምሮ ነበር። የበቃ! የተቃውሞ ሰልፍ እንዳይካሄድ መንግስት አስቀድሞ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን እንደቆየ በአንደንድ ዘገባዎች ተጠቅሷል። ከነዚህም መካከል ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን ማስፈራራት፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ምስጫ ስፍራዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ፣ እና በመካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ እየተካሄደ ስለነበረው ሕዝባዊ ንቅናቄዎች የሚዘግቡ ዜናዎችን ማፈንና የመሳሰሉት ይገኙበታል። በርእዮት አለሙ እና በክስ መዝገቡ ውስጥ በተካተቱ ሌሎች ተከሳሾች ላይ ከቀረቡት የማስረጃ ዝርዝሮች ውስጥ አምስቱ በቀጥታ ከበቃ! ንቅናቄ ጋር የተያያዙ ናቸው። የተወሰኑት የኢ-ሜል መልክቶች፣ የስልክ ጥሪዎች እና እንደ ማስረጃነት የቀረቡ ፎቶዎችም ሳይቀሩ ከበቃ! ንቅናቄ የተቃውሞ ሰልፍ ጥሪ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ታምኗል። የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 30 ላይ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማካሄድ እና አቤቱታዎችን በጋራ ስለማቅረብ እንደተገለጸው "ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው" ይሁንና "አግባብነት ያላቸው ሥርዓቶች" ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች ላይ በሚንቀሳቀስቡባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችገር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ ምብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ሲባል ሊደነገግ ይችላል። ይህም ሰላማዊ ሰልፎችን ለማካሄድ ጥሪ የማድረግ መብት ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና ማግኘቱን ያረግጣል።

ስልሳ ዘጠኙን የኦፌዲን እና ኦህኮ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት አስመልክቶ "የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት" ለሚደረግ ወንጀል "መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆን የማሰናዳት ተግባር" መፈጸማቸውን ለማስረዳት የቀረቡት የጽሁፍ ማስረጃዎች ግጥሞች፣በራሪ ወረቀቶች እና በተከሳሾቹ የተጻፉ ጽሁፎች ናቸው. ከነዚህም ዉስጥ "ከግብጽ ሰላማዊ አመጽ ምን እንማራለን" እና "ኦሮሞ ከባርነት ነጻ ለመውጣት የሚደረግ ትግል ነው" የሚሉት ይገኙበታል። በስልሳ ዘጠኙ ተከሳሾች ላይ ከቀረቡት 48 የጽሁፍ ማስረጃዎች ውስጥ ስላሳ ስምንቱ ተከሳሾቹ በማእከላዊ እስር ቤት እያሉ የሰጡትን የእምነት ቃላት የያዙ ጽሁፎች ናቸው። ከዚህ በታች እንደተመለከተው፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ከእነዚህ የእምነት ቃላት ብዙዎቹ በማስገደድ የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ስጋት አለው።

በአንዱ አለም አራጌ፣ እስክንድር ነጋ አንድ ሌሎች መዝገብ የተከሰሱትን ስምንት ተከሳሾች አስመልክቶ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች አምነስቲ ኢንተርናቲሽናል እስከዛሬ ድረስ ለማግኘት አልቻለም። በሌሉበት ብተከሰሱት 16 ተክሳሾች ላይ ማስረጃ የሚቀርበው ተከሳሾቹ ችሎት ሲቀርቡ እንደሆነ በክሱ ላይ ተገልጿል።

ብዙዎቹ ተከሳሾች ቀደም ሲል ስለሰጧቸው የፖለቲካ አስተያየቶች ወይንም በመንግስት ላይ የሰነዘሩትን ሂስ አስመልክቶ በእስር ላይ ሳሉ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። ለምሳሌ፣ ዘሪሁን ገብረ እግዚያብሄር ፓርቲው ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስላወጣቸው መግላጫዎች እና ለምን ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንደሚነቅፉ በተደጋጋሚ መጠየቃቸውን ገልጸዋል። ርእዮት አለሙም. በምርመራ ወቅት፣ ለኢትዮጵያ ሪቪው ድረ ገጽ ስለምትጽፋቸው ጽሁፎች፤ ለምን የበቃ! ን መፈክር ፎቶ እንዳነሳችና ለሌሎችም እንዳከፋፈለች በተደጋጋሚ መጠየቋን ተናግራለች። በቀለ ገርባና ኦልባና ሌሊሳ ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ተወካዮች ጋር ስለነበራቸው ውይይት እንደተጠየቁ ገልጸዋል። ይሁን እንጂ፤ እነዚህ ታሳሪዎቹ ተጠየቁባቸው የተባሉት ተግባራት በሙሉ ግለሰቦቹ በህገ መንግስትና በአለም አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡትን ሃሳብን በነጻ የመግለጽና የመደራጀት መብታችውን መጠቀማቸውን ለማሳየት በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚገቡ ናቸው።

# ለሽብርተኝነት የተሰጠ ከልክ ያለፈ ሰፊ ትርጓሜ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል የጸረ-ሽብር አዋጁ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በነፃነት ሃሳብን የመግለጽና የመደራጀት መብቶችን ለማፈኛነት እየዋለ ነው የሚል ስጋት አለው።

በ2009 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) ሥራ ላይ የዋለው የጸረ-ሽብር አዋጅ ለሽብርተኝነት ተግባራት የሰጠው ትርጓሜ ሰፊና ግልጽነት የጎደለው ነው። የተወሰኑ ድንጋጌዎች ግልጽነት በጎደለውና ለትርጉም በሚያሻማ መልኩ መቀመጣቸው ሕጋዊ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ የሰብአዊ መብቶች እንቅስቃሴዎች፤ በተለይም በነፃነት ሃሳብን የመግለጽ እና የመደራጅት መብቶች እንደ ወንጀል እንዲቆጠሩ ሊያደርጋቸው ይችላል። እንዲሁም ግለሰቦች የወንጀል ድርጊቶችን ላለመፈጸም ምን ማድረግ ወይንም ከምን ድርጊቶች መቆጠብ እንደሚኖርባቸው አስቀድመው እንዲያውቁ ከላይ የተመለከቱት የአዋጁ እንከኖች አይፈቅዱላቸዉም።

የጸረ-ሽብር አዋጁ አንቀጽ 6፡- “ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት” በሚል ‘የህብረተሰቡ አባላት በከፊል ወይም በሙሉ .... ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈጸም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል’ መልዕክት ማተምን ወይንም ማሳትምን ይከለክላል።’ ይህ ትርጓሜ ከልክ ባለፈ መልኩ ሰፊ ይዘት ያለውና በሰላማዊ መንገድ የሚቀርቡ ተቃዉሞዎችን ሃይልን በመጠቀም ለሚደረግ ዓመፅ ወይንም ተቃዉም ከማነሳሳት ጋር አንድ አድርጎ ይፈርጃቸዋል።[18] ድንጋጌው ጋዜጠኞች በሕገ-ወጥነት የተፈረጁ ድርጅቶችን እንቅስቃሴና ተግባራት በመዘገባቸው ወይም በጽሑፋቸው ውስጥ ሽብርተኞች ተብለው የተፈረጁ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን በመጥቀሳቸው ብቻ ለክስ ይዳርጋቸዋል። ሃያ አራቱም በአንዱዓለም አራጌና በሌሎች’ መዝገብ በተከሰሱት በሃያ አራቱም ተከሳሾች ላይ የቀርበው ክስ በእዚህ የጸረ-ሽብር ሕግ አንቀጽ ላይ የተመሰረተ ነው።

የጸረ-ሽብር አዋጁ አንቀጽ 3 “የሽብር ተግባራት” ተብለው የተከለከሉ ድርጊቶችን ዝርዝር ይዟል። ከእነዚህም መካከል ‘ማናቸውንም የሕዝብ አገልግሎቶች ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆነ’ የሚል ይገኝበታል። ይሁንና አዋጁ ‘ያቋረጠ’ የሚለው አገላለጽ ምን አይነት ድርጊቶችን እንደሚያካትት ግልፅ የማያደርግ ሲሆንእና ሕጋዊ እና ሕገ-ወጥ በሆኑ ድርጊቶች ምክንያት በሚከሰቱ የአገልግሎቶች መቋረጥ መካከል ልዩነት አያደርግም። በሕጋዊ መንገድ በነፃነት የመደራጀት መብትን መሰረት በማድረግ በሚደረጉ እንቅስቃሰዎች ሳቢያ ሊከሰት የሚችል የአገልግሎት መቋረጥን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ሲለዚህ በዚህ ግልጽነት በጎደለው ድንጋጌ ሳቢያ ሰላማዊ ሰልፎችን ተከትሎ የሕዝብ ትራንስፖርት መቋረጥ ቢከሰት ድርጊቱ እንደ ሽብር ተግባር ተደርጎ ይተረጎማል ማለት ነው። ‘በኤልያስ ክፍሌ እና ሌሎች’ መዝገብ አምስቱ ተከሳሾች እንዲሁም በአንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች መዝገብ ሃያ አራቱ (24) ተከሳሾች ክስ የቀረበባቸው ይህንን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነው።

የአዋጁ አንቀጽ 5 ‘ለሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት’ በሚለው ረዕስ ስር የተመለከቱት ክልከላዎች ለሽብር ተግባራት ወይም ለሽብር ድርጅቶች ‘የሙያ፣ የልምድ፣ የሞራል ምክር ወይም ድጋፍ’ ማቅረብንን ያካትታሉ። ከዚህ ውስጥ ‘የሞራል ድጋፍ’ የሚለው ሃሳብ ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ ሕግ ሲረቀቅ በበቂ ሁኔታ ግልጽ እና የጠራ ሆኖ ግለሰቦችም ሕጉ በምን ሁኔታ የሚያከናውኗቸውን

---

[18] ቀድም ባሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ጋዜጠኞች የፍርድ ሂደት ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በሰላማዊ መንገድ በሚደረጉ ትችቶች እና በሰላማዊ ተቃውሞና ኃይል ለተቀላቀለበት ቃውሞ መነሳሳት መካከል ያለውን ልዩነት ከቀሩት የኢትዮጵያ ሕጎች ጋር በማገናዝብ ነጥሎ ለማየት ሲሳናቸው ተስተውሏል። ለምሳሌ ያህል አምነስቲ ኢንተርናሽናል፡- ‘‘Justice Under Fire: Trials of opposition leaders, journalists and human rights defenders in Ethiopia’, በሚል ሐምሌ 29 ቀን 2011 ዓ.ም. ያወጣውን መግለጫ ከዚህ ድኅረ ገጽ ላይ ይመልከቱ፡- http://www.amnesty.org/en/library/info/AFR25/002/2011/en

ተግባራት እንደሚገድብ ሊረዱት በሚችሉት አግባብ መደንገግ እንዳለበት የሚያስቀምጠውንየሕግን እርግጠኛ የመሆንመርህ የሚጥስ ነው።[19] ጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌ፣ መስፍን ነጋሽ እና አብይ ተክለማርያም የተከሰሱት በዚህ አንቀጽ መሰረት ነው።

# እስራቶቹን እና የፍርድ ሂደቶቹን አስመልክቶ በከፍተኛ ደረጃ የተንጸባረቁ ፖለቲካዊ ፍላጎቶች

መንግስት በፍርድ ሂደቱ ላይ ያለውን ለየት ያለ ፍላጎት ያሳየ ሲሆን ከፍተኛ የመንግስት ባልሥልጣናትም ተከሳሾቹ ጥፋተኞች ናቸው በሚል በይፋ መግለጫዎችን ሰጥተዋል።

በጥር ወር ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው ባደረጉት ገለጻ ሁሉም ተከሳሾች ወንጀለኞች መሆናቸውን አስረግጠው ተናግረዋል። በፓርላማው ብቸኛ በሆኑት ገለልተኛው የፓርላማ አባል ግርማ ሰይፉ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው ስለታሰሩት ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ጉዳይ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄ አቅርበውላቸው ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩም በሰጡት ምላሽ መንግስት የተከሰሱት ግለሰቦች በሽብር ተግባር ውስጥ ስለመሳተፋቸው በቂ የሆነ ማስረጃ አለው ማለታቸው ተዘግቧል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው እንደገለጹት "በፍርድ ቤት ወንጀለኝነታቸውን ለማረጋገጥ በቂ የሆኑ ማስረጃዎችን ከማሰባሰባችን በፊት እርማጃ አንወስድም። ሽብርተኞች ስለመሆናቸው ፍርድ ቤቱን ሊያሳምኑ የሚችሉ ማስረጃዎን አሰባስበን እስክናጠናቅቅ ድርስ ምንም አይነት እርምጃዎችን ከመውሰድ ታቅበን ቆይተናል።"

በጥቅምት ወርም 'አፍተንፖስተን' ከተሰኘ የኖርዌይ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ ጠቅላይ ሚንስትሩ የሲውዲን ጋዜጠኞች የሆኑት ሽቢ እና ፐርሰን የሽብርተኞች ተባባሪዎች እንደሆኑ ሲገልጹ የተናገሩት *"እጅግ ቢያንስ የሽብርተኛ ድርጅት ተላላኪዎች ናቸው። በፍጹም ጋዜጠኞች አይደሉም።"*

የተቀሩት የመንግስት ባለሥልጣናትም በተከታታይ በሚሰጧቸው አስተያየቶች ተከሳሾቹ ወንጀለኞች መሆናቸውን ነው የሚገልጹት። ይህ አባባላቸው በእስር ላይ የሚገኙትን ጋዜጠኞች እና ለሎች ታዛቢዎችንም ያካትታል። ለምሳሌ ያህል በሰኔ ወር ውብሸት ታዮ፣ ርእዮት አለሙ፣ ዘሪሁን ገብረእግዚያብሔር እና ደጀኔ ተፈራ መታሰራቸውን ተከትሎ የመንግስት ቃል-አቀባዩ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለጹት አራቱም የታሰሩት በሽብር ተግባር ውስጥ ሲሳተፉ ስለተገኙ ነው የሚል ነበር። ቃል-አቀባዩ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል አስረግጠው እንደተናገሩት መንግስት በሁሉም ታሳሪዎች ላይ በሕዝብ ዘንድም ሆነ በፍርድ ቤት ወንጀለኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ 'ተጨባጭ ማስረጃዎችን' አዘጋጅቶ የያቀርባል ብለዋል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል እንዲህ ያሉት በከፍተኛ ባለሥልጣናት የሚሰጡ አስተያየቶች ቀድሞውንም ገለልተኝነት በጎደለው የፍትህ አካል ላይ የፖለቲካ ጫናን ያሳድራሉ የሚል ስጋት አለው። የኢትዮጵያ የፍትሕ ሥርዓት በከፍተኛ ሁኔታ ፖለቲካዊ አቅጣጫን የያዘ በመሆኑ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ያለው የሥራ ዋስትና፤ በከፍተኛ ደረጃ ያሉትን የስራ መደቦች ጨምሮ፣ የገዥው

[19] ማንኛውም ሃሳብን በመግለጽ ነፃነት ላይ የሚደረግ ገደብ "እንደ 'ሕግ' ሊቆጠር የሚችለው ግለሰቡ የራሱን ወይም የራሷን ተግባራት በተገቢው ሁኔታ ለመከውን እንዲችል ወይም እንድትችል ለማድረግ አጥጋቢና በቂ ጥንቃቄ ተደርጎበት የተዘጋጀ እንደሆነ ብቻ ነው" የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ ቁ. 34፣ ምዕራፍ 25፣ አንቀጽ 15(1)። የዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳን አንቀጽ 15(1) ላይም የወንጀል ክሶች ሕጋዊነትን በተመለከተ በያዘው ጠቅላላ መስፈርቶች ላይ ተለይቶ እንደተቀመጠው "ማንምኛውም ሰው በአገሩ ወይም በዓለም አቀፍ ሕጎች ላይ በግልጽ የወንጀል ተግባር እንደሆነ ድርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ ተለይቶ ባልተደነገገ ማንኛውም ድርጊት ወይም አንድን ነገር አለማድረግ የተነሳ በወንጀል ሊቀጣ አይችልም"

ፓርቲ አባል ከመሆን ጋር የተቆራኙ ናቸው። በተለይም በግል ከፍተኛ የሆነ ተሰሚነት ያላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጡዋቸው አስተያየቶች እጅግ አሳሳቢ ናቸው።

አምነስቲ ኢንተርናሽናልን በተጭማሪ ያሳሰበው ጉዳይ እነዚህ በከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚሰጡት አስተያየቶች የተከሳሾቹን ከፍርድ ውሳኔ ጥፋተኝነታቸው እስከሚረጋግጥ ድረስ በሕግ ፊት ንጹሕ ሆኖ የመገመት ሕገ-መንግስታዊ መብታቸውን ሊጥስ መቻሉ ነው።[20] የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ እንዳስቀመጠውየመንግስት ባለሥልጣናት *"በፍርድ ሂደት ላይ ባሉ ጉዳዮች ቅድመ-ፍርድከመስጠት መታቀብ አለባቸው፤ ለምሳሌ በጉዳይ ላይ በይፋ በሚሰጡት መግለጫ የታሳሪዎቹን ጥፋተኛነት ከሚያረጋግጡ አስተያየቶች መታቀብ አለባቻል።"*[21]

ከፍተኛ ባለስልጣናት ተከሳሾችን ወንጀለኞች አድርጎ በማቅረብ ከሚሰጡት አስተያየቶች በተጭማሪ መንግስት ይህ የአፈና ዘመቻ ሊቀጥል እንደሚችል ፍንጮችን አሳይቷል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በይፋ እንደገለጹት ታዋቂ የሆኑትን ጨምሮ በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና አመራሮችን የማሰር ሃሳብ በመንግስት በኩል ያለ መሆኑን ነው። የመንግስት እርምጃ በሽብር ወንጀለኝነት በታሰሩት ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፓርቲ አባልት ላይ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን በቀጣይም በቀሩት በርካታ ግለሰቦች ላይ መንግስት በቂ የሆኑ ማስረጃዎችን እያሰባሰበ ሲሆን እንዳጠናቀቀም ሌላ ዙር እስር እንደሚኖር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጥቅምት ወር ለፓርላማው ገልጸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት *"በሽብር ተግባራት የተሰማሩ ወይም ከአሸባሪ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እንዳላቸው የደረስንባቸው ሌሎች በርካታ ሰዎች አሉ። እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት እየጠበቅን ያለነው በቂ የሆነ ማስረጃ እስከናሰባስብ ድረስ ነው።"* ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም በቀጣይ ዙር የሚታሰሩት ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የተወሰኑ የመድረክ (የስምንት ዋና ዋና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥምረት የሆነው የኢትዮጵያዊያን ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ) ከፍተኛ አመራር አባላት ይገኙበታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በእነዚህ ግለሰቦች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑን ቢያምኑም በሽብርተኝነት ተግባር ወንጀለኞች ናቸው ከማለት ሳይቆጠቡ የሚከተለውን ብለዋል፤ *"በሽብር ተግባራት መሰማራታቸውን ልባችን ያውቀዋል። ይሁንና ይህ ብቻውን ጉዳይን ወደ ፍርድ ቤት ለማድረስ በቂ አይሆንም።"*

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የታየው ከፍ ያል የፖለቲካ አትኩሮት አጠንክሮ የሚያሳየው በታሳሪዎቹ ላይ የመንግስት የፖለቲካ ኢላማ ያነጣጠረባቸው መሆኑን እና የመታሰራቸውም ሆነ የተመሰረተባቸው ክስ መሠረቱ ሰላማዊ እና ሕጋዊ በሆነ መልኩ የተለዩ አስተሳሰቦቻቸውን መግለጻቸው ነው።

[20] የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 20.
[21] የተባበሩት መንግስታት የሰባዊ መብቶች ኮሚቴ፤ ጠቅላላ አስተያየት 32፣ ምዕራፍ 32

# ክፍል ሦስት፡- ከፍርድ ሂደቱ መጀመር በፊት በእስር ቤት የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶች

# በእስር ላይ እንዳሉ በቤተሰቦቻቸው እንዳይጎበኙ መከልከል

መታሰራቸው በዚህ መግለጫ ወስጥ የተጠቀሰው ሁሉም የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ከተያዙ በኋላ በመጀመሪያ ተወስደው የታሰሩት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘውና ማዕከላዊ ተብሎ በሚጠራው የፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ እና ክትትል መምሪያ ነው። በከፍተኛ ወንጀሎች የተጠረጠሩ እና የፖለቲካ ተቃሚዎች ጭምር ብዘውን ጊዜ የሚታሰሩት በማዕከላዊ ነው። ባለፉት ጊዜያት እጅግ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ለተደጋጋሚ ጊዜያት በእዚህ ስፍራ ታስረዋል። ከእነዚህም መካከል አንዱዓለም አራጌ እና እስክንድር ነጋ ይገኙበታል። በማዕከላዊ እስር ቤት የእስረኞች መብት እንደማይከበርና በተልምዶም ግርፋትና የማሰቃየት ተግባር በምርመራ ሂደት እንደሚፈጸም በተደጋጋሚ እንደሚገለጸው ይነገራል።

በእስር ላይ የሚገኙትና ክስ የቀረብባቸው መቶ ሰባት (107) የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ክስ ከተመሰረተባቸው በኋላ ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው የቃሊቲ ማረሚያ ቤት ተወስደዋል።

የታሳሪዎች ከሌሎች ጋር የመገናኘትና እና ጎብኝዎችን የመቀበል መብት እንደ ማሰቃየት፣ ሌሎች በደሎችና መሰወርን የመሳሰሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በታሳሪዎቹ ላይ እንዳይፈጸሙ የመከላከያ ዋነኛ መንገድ ነው። ታሳሪዎች ተገቢና ሁኔታ አስፈላጊ የሆነ ቁጥጥር ብቻ ተደርጎባቸው ከእስር ውጭ ካለው ዓለም ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ሊፈቀድላቸው ይገባል።[22]

ከመቶ አሥራ አራቱ ታሳሪዎችቢያንስ መቶ አምስት (105)[23] የሚሆኑት ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በማዕከላዊ እስር ቤት በነበራቸው የመጀመሪያው የአንድ ወር ቆይታ በቤተሰቦቻቸው እንዳይጎበኙ ተደርገዋል። አንዳንዶቹ ከዚያም በላይ ለሆነ ጊዜ ከሌሎች ተገልለው ብቻቸውን በመታሰር በቤተሰቦቻቸው እና በጠበቆች እንዳይጎበኙ ተደርገዋል።ይህ ሁኔታም በታሳሪዎቹ ላይ የማሰቃየት፣ ሌሎች በደሎች ወይም የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች ሊፈጸሙ የሚችሉበትን ሁኔታ ከፍ አድርጎታል።

የዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር ቤተሰቦች ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ወራት ያህል እንዳይጎበኙት ተከልክለዋል። በመጋቢት ወር ተይዘው ከታሰሩት የኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆች መካከል የአንዱ ታሳሪ ቤተሰቦች ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለጹት ከታሰረበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት ወራት ያህል ወንድሙ እንዳያየው ተደርጓል።

ከታሳሪዎቹ መካከል የአንደኛው ባለቤት በአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ባለቤቷን ለመጎብኘት የተፈቀደላት ለሦስት ጊዜያት ብቻ እንደሆነ ተገልጿል። የሌላ ታሳሪ ሚስት ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለጹት ማዕከላዊ እስር ቤት የሚገኙትን ባለቤታቸውን ለመጎብኘት ጥያቄ በማቀረባቸው የተነሳ እሳቸውም ሊታሰሩ እንደሚችሉ ማስፈራሪያ ደርሶባቸዋል። በብዙዎቹ ጉዳዮች

---

[22] በተባበሩት መንግስታት በማናቸውም ሁኔታ፤ በማቆያዎችም ሆነ በእስር ቤቶች ለሚገኙ እስረኞችን ተገቢውን ጥበቃ የማድረግ መርሆዎች (መርህ 19) (በ1988 ዓ.ም. እ.አ.አ በተ.መ. ጠቅላላው ጉባዔ የጸደቀ)

[23] አምነስቲ ኢንተርናችናል ከመቶ አሥራ አራቱ (114) መካከል ስለቀሩት ዘጠኝ ሰዎች በዚህ ጉዳይ መረጃ ለማግኘት አልቻለም

ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደተገለጸው ቤተሰቦቻቸው የታሰሩባቸው የቤተሰብ አባላት ታሳሪዎቹ የት እንደሚገኙ ምንም ሳይገለጽላቸው እስከ ሁለት ወራት ያህል ቆይተዋል።

አብዛኛዎቹ የኦፌዴን እና ኦሕኮ ፓርቲዎች አባላት ከመላው የኦሮሚያ ክልል፤ አንዳንዶቹ ከ200 እስከ 300 ኪ.ሜ ርቀት ካላቸው የመኖሪያ ስፍራቸው ተይዘው ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደርጓል። ይህም ማለት ቤተሰቦቻቸው ከእርቀቱ የተነሳ እስር ቤት ሄደው ሊጠይቋቸው አይችሉም ነበር።

ሌሎች ደግሞ ከመነሻውም ከሌሎች እስረኞች ተነጥለው ብቻቸውን የታሰሩ ሲሆን በቤተሰቦቻቸውም እንዳይጎበኙ ተደርገዋል። ለምሳሌ ያህል ዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር፣ ዉብሸት ታዮ፣ ርእዮት አለሙ እና እስክንድር ነጋ፤ ሁሉም ለየብቻቸው ተገልለው በተያዙበት ሰሞን በተለያየ ክፍል ውስጥ እንዲቆዩ ተደርገዋል።

የአብዛኛዎቹ ታሳሪዎች ቤተሰቦች ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንዳመለከቱት በቤተሰብ እንዲጎበኙ ከተፈቀደም በኋላ በርካታ ገደቦች ይጣልባቸው ነበር። በአንዳንድ ሁኔታዎች ለጉብኝት ይፈቀድላቸው የነበረው የአምስት ደቂቃ ቆይታ ብቻ ነበር። በቤተሰብ ጉብኝት ወቅትም አንድ ወይም ሁለት ፖሊሶች በቅርብ እንዲቆሙ በማድረግ የግል ውይይቶችን ማካሄድ ይከለከል ነበር። በአንዳንድ ሁኔታዎችም በተለይም እንደማሰቃየት ያሉ አጠያያቂ ጉዳዮችን በሚያነሱበት ጊዜ ፖሊሶቹ ጣልቃ በመግባት ውይይቶችን አስቁመዋል። አንዳንድ ታሳሪዎች ቤተሰቦቻቸው ሊጎበኙዋቸው ሲመጡ በምን ጉዳይ ላይ ብቻ ማውራት እንዳለባቸው በቅድሚያ በጠባቂዎቻቸው መመሪያ እንደተሰጣቸው ተናግረዋል። በጥቅምት ወር ውብሸት ታዮ እና ዘሪሁን ገብረእግዚያብሔር የጉብኝት ፕሮግራማቸው የተቀየረ መሆኑን ተገልጾላቸዋል። ከእዚያም በኋላ ጠያቂዎች  ሁለቱን ሰዎች ለመጎብኘት ይፈቀድላቸው የነበረው  በቀን ለአሥር ደቂቃዎች ብቻ ነው። አንዳንድ የኦፌዴን እና ኦሕኮ ታሳሪዎችን የሚጎበኙ ቤተሰቦች ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለጹት ተመሳሳይ የሆነ የአሥር ደቂቃ ገደብ በነሱም ላይ ተጥሎአል።

አንዳንድ ጊዜም ቤተሰቦች ክስ ከመመስረቱ በፊት የነበሩ የፍርድ ቤት ውሎዎችን እንዳይከታተሉ ይታገዱ ነበር። አንድ የቤተሰብ አባል በሽብር ጉዳይ ሌሎች የችሎት ታዳሚዎች መግባት እንደማይችሉ በፍርድ ቤቱ ሠራተኞች እንደተነገረው ገልጿል። በተደጋጋሚ ጊዜያት የታሳሪዎቹ ሚስቶች ወይም ቤተሰቦች ጉዳዩ ወደሚታይበት ችሎት እንዳይገቡ ሞልቷል በሚል ምክንያት ተከልክለዋል። የአንድ ታሳሪ ሚስትም ምክንያቱ ሳይገለጽላቸው ወደ ችሎቱ እንዳይገቡ ተከልክለዋል። በተደጋጋሚ ጊዜያትም ቤተሰቦች የታሰሩባቸውን ሰዎች የፍርድ ሂደት እንዳይከታተሉ ለማድረግ በማሰብ ችሎቱ ለመሰየም ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀረው ችሎቱ የሚካሄድበት ሰዓትና ቀን እንዲቀየርር ተደርጓል። አንድ የቤተሰብ አባል ወደ ችሎት ለመግባት ስትሞክር በፖሊስ ተመታለች።

# ጠበቃ የማግኘት መብትን መነፈግ

በእስር ላይ ለሚገኙ ሰዎች በወቅቱና በመደበኛ ሁኔታ በጠበቆቻቸው መጎብኘት መቻላቸው በእስር ቤት ወስጥ ሊደርሱባቸው የሚችሉትን የማሰቃየትና ሌሎች በደሎች፣ በግዳጅ የእምነት ቃላቸውን እንዲሰጡ መገደድ እና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸምባቸው ለመከላከል እጅግ ይረዳል።[24] የጸረ-ስቃይ ኮሚቴው በቅርቡ ለኢትዮጵያ በሰጠው ማሳሰቢያ እንደገለጸው "...

[24] የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ አስተያየት 20፣ ምዕራፍ 11፣ የጸረ-ስቃይ ኮሚቴ ጠቅላላ አስተታየት ቁ.2 ምዕራፍ 13፣ የተባበሩት መንግሥታት የማሰቃየት ተግባራትን የሚመለከተው ልዩ ራፖርተር (E/CN.4/2003/68) ታኅሳስ 17 ቀን 2002 ዓ.ም. (እ.አ.አ) ምዕራፍ 34፣ በተባበሩት መንግስታት በማናቸውም ሁኔታ፤ በማቆያዎችም ሆነ በእስር ቤቶች ለሚገኙ እስረኞች ተገቢውን ጥበቃ የማድረግ መርሆን የሚመለከተው አካል (መርህ 17 -18)፣ በተባበሩት መንግስታት የጠበቆችን ሚና በሚመለከተው መሰረታዊ መርሆች ምዕራፍ 7

አፋጣኝና አጥጋቢ በሆነ መልኩ መንግስት ሁሉም ታሳሪዎች በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ጊዜ አንስቶ መሰረታዊ የሆኑት የሕግ ጥበቃዎች በሙሉየሚደረግላቸው መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህም ሁኔታ፤ በተለይም የእስረኞችን መብት በተመለከት፡- ... በወቅቱ ጠበቃ የማግኘት መብትን” ያካትታል።[25]

በተጨማሪም በወቅቱና በመደበኛ ሁኔታ በጠበቆቻቸው የመጎብኘት ዕድል “ፍትሐዊ የሆነ የፍርድ ሂደት ኢንዲኖር እና በፍርድ ሂደቱም ውስጥ በእኩል የመከራከር ዕድል የማግኘት መርሆን ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል አስፈላጊ ነገር ነው።”[26] የአለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳን እንደሚደነግገው ሁሉም ክስ የተመሰረተባቸው ሰዎች “የክስ መከላከያቸውን ለማዘጋጀት በቂ ነው ተብሎ የሚገመት ጊዜ እና ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው እንደሚገባና አማካሪዎቻቸውን የመምረጥና የመገናኘት” መብት ያላቸው መሆኑን ነው።

በጥቂት ጉዳዮች የሕግ ጠበቆች ታሳሪዎችን በተያዙበት ሳምንት ውስጥ ለመጎብኘት ሙከራ አድርገዋል ሆኖም በሞከሩባቸው ጊዜያቶች ሁሉ ታሳሪዎቹን እንዳያገኙ ተከልክለዋል። በዚህ ሪፖርት ከተጠቀሱት መቶ አሥራ አራቱ  ታሳሪዎች መካከል እጅግ አብላጫዎቹ ከታሰሩበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ወር እስከ ሦስት ወራት ለሚደርሱ ጊዜያቶች የሕግ ባለሙያ እንዳያገኙ ተከልክለው ነበር። ይህም አብዛኞዎቹ ታሳሪዎች ክስ ሳይመሰረትባቸው እና ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በእስር የቆዩበት ወቅት ነው። ብዙዎቹ ታሳሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ጠበቃ ማግኘት የቻሉት የፍርድ ሂደቱ በተጀመረበት የመጀመሪያው ዕለት መንግስት ጠበቃ ሲያቀምላቸው ነበር። ይህም ማለት አንዳንድ በመጋቢት እና ሚያዚያ ወር የታሰሩት የኦሕኮ እና የኦፌዴን አባላት ከታሰሩበት ጊዜ አንስቶ ለአራት ወራት ያህል የሕግ ባለሙያ ጨርሶ እንዳያገኙተደርገዋል።

ሊከተሉ የሚችሉ የቅጣትና የማዋከብ መዘዞችን በመፍራት የግል ጠበቆች ከፖለቲካ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ የታሰሩ ግለሰቦችን ከመወከል የሚታቀቡበት ሁኔታ አለ። ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳዮች ቀደም ሲል ታሳሪዎችን የወከሉ ጠበቆች ቀላል የማይባል ማዋከብ ደርሶባቸዋል። የታሳሪዎቹ ቤተሰቦች ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለጹት ጠበቆቹ ሊደርስብን ይችላል በለው ከፈሩት መዘዝ የተነሳ የታሰሩ ወገኖቻቸውን ሊወክሉ የሚችሉ ጠበቆችን ለማግኘት ከፍተኛ ችግር ገጥሟቸውዋል።

# ማሰቃየትና ሌሎች ዓይነት በደሎችን ማድረስ

ጋዜጠኞችንና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ በሌሎች ታሳሪዎች ላይ በማዕከላዊ እስር የማሰቃየት እርምጃዎች እንደሚፈጸሙ በተደጋገሚ ጊዜያት ተገልጿል። በነሐሴ ወር አምነስቲ ኢንተርናሽናል ማዕከላዊ የሚገኙ ታሳሪዎችን ለመጎብኘት ተደጋጋሚ ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም ጥያቄው በባለሥልጣናት ውድቅ ተደርጓል።

ከላይ እንደተገለጸው ታሳሪዎች በጠበቆቻቸው እና በቤተሰቦቻቸው አባላት እንዳይጎበኙ መከልከል ታሳሪዎቹ ሊደርስባቸው የሚችለውን የስቃይና የተለያዩ በደሎች አደጋ እጅግ ከፍ ያደርገዋል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል በዚህ መግለጫ ስለተጠቀሱት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ያሰባሰባቸው ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት አብዛኞዎቹ ታሳሪዎች ለስቃይና ለተለዩዩ በደሎች የተዳረጉ መሆኑን ነው። በሁሉም ታሳሪዎች ላይ የማሰቃየት እና ሌሎች በደሎች የደረሰባቸው እንደተገለጸው በቤተሰቦቻቸው እንዳይጎበኙ በተከለከሉባቸው ጊዜያቶች ውስጥ ነው።

---

[25] ኢትዮጵያን በተመለከተ የጸረ-ስቃይ ኮሚቴው የግምገማ ማጠቃለያ፡ UN Doc.CAT/C/ETH/CO/1, ጥር 20 ቀን 2011, ምዕራፍ.12.

[26] የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ ጠቅላላ አስተያየት 32፣ ምዕራፍ 34

ታሳሪዎቹ እራሳቸው እንደገለጹትም ከተያዙበት ጊዜ አንስቶ በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት ሳምንታት ውስጥ ምርመራ ተካሂዶባቸዋል። ከመቶ አሥራ አራቱ ውስጥ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ታሳሪዎች ማዕከላዊ በነበሩበት ጊዜ በምርመራ ወቅት ማሰቃየትና የተለያዩ በደሎች ይደርስባቸው እንደ ነበር አቤቱታ አሰምተዋል። ይህ አይነቱ አቤቱታ በተለይም በኦሕኮ እና ኦፌዴን አባላት ተደጋግሞ ቀርቧል። ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል የደረሱት ጥቆማዎች መሰረት በታሳሪዎች ላይ የሚደርሱ ማሰቃየትና በተለያየ መልኩ የሚፈጸሙት በደሎች የሚከተሉትን ይጨምራል፡ ድብደባ፣ እርግጫና ጡጫ፣ ወንበር፣ በሽቦ፣ በብረት ቁራጮችና በሌሎች የተለያዩ ቁሳቁሶች ግርፋትና ድብደባ ፣ እጆቻቸውን የፊጥኝ አስሮ ከግርግዳ ወይም ከጣሪያ ላይ መስቀል፣ እንቅልፍ መከልከል፣ እጅግ ለረዥም ሰዓትአካላዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ ማስገደድ፣ ለእረዥም ጊዜያት ለብቻ ማቆየት እና ምንም ብርሃን በሌለባቸው ጨለማ ክፍሎች ውስጥ ማቆየት።

በርካታ ታሳሪዎች ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለጹት እጆቻቸው ከጭንቅላታቸው በላይ ከግርግዳ ጋር ታስረው ለሁለት ወይም ሦስት ቅናት ያህል እየተገረፉ እንዲቆዩ ተደርገዋል። አንድ የቀድሞ ታሳሪ በእስር ቤት እያለ በደረሰበት ተመሳሳይ ድርጊት ምክንያት በክርኑና በመዳፎቹ መካከል ባለው የሰውነቱ ክፍል ዙሪያ የሚታየውን ወደ ውስጥ የሰረጎደ የቁስል ጠባሳ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል አሳይቷል። የተወሰኑ ታሳሪዎችም እንደገለጹት በመጀምሪያዎቹ የእስራት ጊዜያት ውስጥ ምንም ዓይነት ብርሃን በሌለባቸው ጨለማ ክፍሎች ውስጥ ጊዜይት አንዳንዴ ሁለት ሳምንት ያህል እንዲቆዩ ተደርገዋል።

የተወሰኑ ታሳሪዎችም እንደገለጹት ማዕከላዊ እስር ቤት ውስጥ በተካሄደባቸው ምርመራ የኢ-ሜሎቻቸውን የሚስጢር መለያ ቃል እንዲሰጡ ተገደዋል። የተወሰኑት ይህን የመለያ ቃል እንዲሰጡ በተደጋጋሚ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል። ሌሎች ጥቂቶች ደግሞ የቃላት ዘለፋ፣ ውክቢያና ማስፈራሪያ ደርሶባቸዋል። በበርካታዎቹ ጉዳዮች የግለሰቦች የኢ-ሜይል ሰነዶችም በቀረበባቸው ክስ ላይ እንደ ማስረጃ ተያይዘው ቀርበዋል።[27]

ቁጥራቸው የተወሰኑ ታሳሪዎች በደረሰባቸው በእነዚህ ጥቃቶች የተነሳ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። እነዚህ ጉዳት የደረሰባቸው ታሳሪዎችም በማዕከላዊ እስር ቤት እያሉ ሕክምና እንዳያገኙ ተከልክለው ቆይተዋል።

በመጋቢት እና ሚያዝያ ወር ውስጥ ከታሰሩት የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት መካከል በርካታዎቹ በመላው የኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ስፍራዎች ታስረው ከቆዩ በኋላ ነው ወደ አዲስ አበባ የተዛወሩት፤ የተወሰኑት ከ200 እስከ 300 ኪ.ሜ. እርቀት ካላቸው ስፍራዎች የተያዙ ናቸው። አንዳንድ አሁን ከእስር የተለቀቁ ታሳሪዎች እና የቤተሰብ አባሎቻቸው ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለጹት ከምዕራብ ኦሮሚያ የተያዙ ታሳሪዎች መጀመሪያ የተወሰዱት ለአዲስ አበባ ቅርብ ወደ ሆነው አምቦ ከተማ ነው። ታሳሪዎቹ ለተወሰነ ጊዜ በአምቦ ከተማ ውስጥ በሚገኝ ስውር እስር ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ተደርጎ ክፉኛ ተደብድበዋል። በሕግ ባልታወቁ ስውር እስር ቤቶች የሚደረጉ እስራቶች ታሳሪዎቹኝ የስቃይ እና ሌሎች በደሎች ክፉኛ ያጋልጣቸዋል።

በተመሳሳይ ጊዜ ወስጥ የተወሰኑ ሌሎች የኦሕኮ እና የኦፌዴን አባላት በሕገ-ወጥ መንገድ ከተያዙ በኋላ እረዘም ላሉ ጊዜያት በሌሎች ሕጋዊ ባልሆኑ የማሰሪያ ስፍራዎችን ታስረው ቆይተዋል። አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ለሦስት ሳምንታት ያህል ሕጋዊ ባልሆነ ስፍራ ታስሮ የቆየ መሆኑን እና በእሱ ግምትም የታሰረው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንደሆነ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ገልጿል። በእስሩም ወቅት ለተደጋጋሚ ጊዜያት ድብደባና ውስጡ ብረት ባለው ሽቦ ተገርፏል። በግርፋቱ ሳቢያ ደረሰብኝ ያለውን ጉዳት በሰውነቱ የተለያዩ ክፍሎች ያሉትን ጠባሳዎች ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል አሳይቷል። በእስር ላይ እንዳለ በደረሰበት የድብደባ ጉዳት የተነሳ ከእስር ከተለቀቀ በኋላ ሆስፒታል ተኝቶ ለመታከም ተገዷል።

---

[27] ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደቀረቡት ጥቆማዎች የብርሃኑ እምሩ የፍርድ ሂደት ላይ የኢ-ሜል መልዕክቶች በራሱ ላይ እንደ ማስረጃ የቀረቡበት ሲሆን ቆይቶም እንደተረጋገጠው የተፈበረኩ መሆናቸው ተረጋግጧል። ኢ-ሜሉ ከብርሃኑ የኢ-ሜል አድራሻ የተላከ ሲሆን የተላከውም እሱ በማዕከላዊ እስር ላይ በነበረበት ወቅት ነ፡፡ ኢ-ሜሉም ከማስረጃ ዝርዝር ውስጥ እንዲወጣ ተደርጓል።

የተወሰነ ቁጥር ያለቸው እስረኞችም የክስ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በማዕከላዊ እስር ቤት ውስጥ ለስቃይና ሌሎች በደሎች መዳረጋቸውን ለዳኞች አቤቱታ አቅርበው ነበር። በሚያዚያ ወር የታሰሩት የኦፌዴን አመራር አባል የሆኑት ብርሃኑ እምሩ በተደጋጋሚ ጊዜያት ድብደባና ኢ-ሰብዓዊ እና ለሰው ልጅ ክብር በማይገባ አኳኋን የማሰቃየት ተግባር በማእከላዊ እስር ቤት እንደተፈጸመባቸው የክስ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በዋለ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ ሳይቀበል ውድቅ እንዳረገው ተገልጿል።

በነሐሴ ወር የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የሆኑት ዘሪሁን ገብረእግዚያብሔር እና ጋዜጠኛ ውብሸት ታዮ ሁለቱም ከክሱ መጀመር በፊት በችሎት ባቀረቡት አቤቱታ በማዕከላዊ እስር ቤት ማሰቃየት የደረሰባቸው መሆኑን ገልጸዋል።[28] ዘሪሁን እንደገለጸው በተፈጸመበት ግርፋት የተነሳ የጎድን አጥንት ስብራት እና የጆሮ ህመምን ጨምሮ ሌሎች የአካል ጉዳቶች የደረሱበት መሆኑግ ገልጾ የሕክምና እርዳታ እንዲደረግለት ለፍርድ ቤቱ አመልክቷል። ፍርድ ቤቱ ውብሸት ያቀረበውን አቤቱታ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ማጣሪያ ሳያደርግ ውድቅ ማድረጉ ተገልጿል። በዘሪሁን በኩል ለቀረበው አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ደረሰብኝ ያለው በደል እንዲቆም ተዕዛዝ በመስጠት ለሕክምና ወደ ሆስፒታል እንዲወሰድ ትዛዝ አስተላልፏል። ምንም እንኳን ዘሪሁን ከዚህ የፍርድ ቤት ውሎ በኋላ የማሰቃየት ተግባር የተፈጸመበት ባይሆንም ለሕክምና ወደ ሆስፒታል እንዲሄድም ሆነ ዶክተር እንዲጎበኘው አልተፈቀደለትም። እንደተናገረውም ማዕከላዊ በሚገኙት ጠባቂ ፖሊሶች "ለሽብርተኞች የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት የለም" የሚል ምላሽ ተሰጥቶታል። በህዳር ወር ዘሪሁን ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ከተዛወረ በኋላ በስተመጨረሻ በነርስ እንዲታይና ለደረሰበት የአካል ጉዳቱም ሕክምና እንዲያገኝ ተደርጓል።

ህዳር 10 ቀን ናትናኤል መኮንን የእሱና አብሮት የተከሰሰው ሰው ክስ በሚሰማበት ወቅት ለፍርድ ቤቱ ባሰማው አቤቱታ በእስር ቤት ውስጥ በተከታታይ የማሰቃየት ተግባርና ሌሎች በደሎች እንደ ደረሱበት ገልጿል። ናትናኤል እንደገለጸው በተደጋጋሚ ጊዜያት ድብደባ የተፈጸመበት ሲሆን ለ23 ቀናትም እንቅልፍ እንዳይተኛ ተደርጓል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ለመረዳት እንደቻለው የተጠቀሱትን የማሰቃየት ተግባራት አስመልክቶ በቀረቡት አቤቱታዎች ላይ ወይም የድርጊት ፈጻሚዎቹን ማንነት ለይቶ ለማወቅ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ምርመራ አልተካሄደም። አምነስቲ ኢንተርናሽናል እነዚህን በደል ስለመፈጽማቸው የሚገልጹ አቤቱታዎች በማንሳት ከተለያዩ የመንግስት ባልስልጣናት ጋር ተወያይቶባቸዋል። በእያንዳንዱ አጋጣሚ ያነጋገራቸው የመንግስት ባለስልጣናት የሰጡት ምላሾች በተለያየ መልኩ ቢገለጹም አንድ ይዘት ያላቸው ናቸው፡ ይኸውም በማዕከላዊ እስር ቤት ውስት የማሰቃያት ድርጊት አይፈጸምም የሚል ነው። ይሁንና እነዚህን ጨምሮ ሌሎች አቤቱታዎች ተጣርተው የማያውቁ መሆኑን አምነዋል። በነሐሴ ወር አንድ የፍትሕ ሚኒስቴር ባለስልጣን ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ይህንኑ ጉዳይ በማስመልከት እንደገለጹት በማዕከላዊ ውስጥ የማሰቃየት ተግባር ተፈጽሟል በሚል የሚቀርቡትን አቤቱታዎች ማጣራት እንደማያስፈልግ ገልጸው ምክንያቱንም ሲያስረዱ በማዕከላዊ ውስጥ ይህን ዓይነቱ ተግባር እንደማይፈጸም ስለሚያውቁ መሆኑን ገልጸዋል።[29]

# ማሰቃየትና ሌሎች ዓይነት በደሎችን በመፈጸም የተገኙ ማስረጃዎች

አምነስቲ ኢንተርናሽናል በደረሱት መረጃዎች በስድስቱ የክስ መዝገቦች ውስጥ ከተከሰሱት በርካታዎቹ ታሳሪ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች በከፍተኛ ጫና ስር ሆነው በተዘጋጀ የእምነት ቃል ላይ እንዲፈርሙ ወይም በራሳቸው ላይ እንደ ማስረጃ

[28] ሁሉቱ ሰዎች በሰኔ ወር ከታሰሩበት ዕለት አንስቶ ክስ እስከ ተመሰረተባቸው መስከረም ወር ድረስ በማዕከላዊ እስር ቤት ከቆዩ በኋላ ወደ ቃሊቲ ተዛውረዋል።

[29] ነሐሴ 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ከፍትህ ሚኒስቴር ባለስልጣናት ጋር ባደረገው ስብሰባ

በሚቀርቡ ሰነዶች ላይ እንዲፈርሙ ተገደዋል። 'በተሻለ በካሺ እና ሌሎች' የክስ መዝገብ ውስጥ ከተከሰሱት ከስልሣ ዘጠኙ የኦፌዴን እና የኦሕኮ ፓርቲዎች አባላት መካከል በሰላሳ ስምንት (38) ታሳሪዎች ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች የታሳሪዎቹን የእምነት ቃል እንደሚጨምር በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ ተመልክቷል። እንደ ኦሕኮ ፓርቲ ኃላፊዎች ገለጻ አብዛኛዎቹ ታሳሪዎች በኃይል ተገደው በተዘጋጀ የእምነት ቃል እንዲፈርሙ ተደርገዋል።

በሌሎቹ መዝገቦች ከተከሰሱት መካከል አንድ ታሳሪ እንደገለጸው በምርመራ ወቅት በግዳጅ እራሱን ለመወንጀያነት በተዘጋጁ የተለያዩ ሰንዶች ላይ እንዲፈርም እና የእሱ መሆናቸውንም እንዲያምን የማስገደድ ሙከራ ተደርጎበታል። ሌሎች ሁለት ታሳሪዎችም የኢ-ሜሎቻቸውን መክፈቻ ቃል ተገደው እንዲሰጡ ማሰቃየት ደርሶባቸዋል። ከሁለቱም ታሳሪዎች የተገኙ የኢ-ሜል መልዕክቶች ልውውጦች በማስርጃነት ከክሱ ዝርዝር ጋር ተያይዘው ቀርበዋል። ሁለት ሌሎች ታሳሪዎች ደግሞ በምርመራው ወቅት አብረዋቸው በታሰሩ ሰዎች ላይ እንዲመሰክሩ ከፍተኛ የሆነ ጫና እንደተደረገባቸው ተገልጿል።

## በማሰቃየትና ሌሎች ዓይነት በደሎችን በመፈጸም የሚገኙ ማስረጃዎች ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ

የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ማሰቃየት ድንጋጌ አንቀጽ 15 በግልጽ እንዳስቀመጠው ማንኛውም ሰዎችን በማሰቃየት የሚገኝ ቃል በማንኛውም የፍርድ ሂደት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።[30] የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስትም እንደሚደነግገው "የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።"[31] ይሁንና በማሰቃየት የተገኙ የእምነት ቃል እና ሌሎች መረጃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በማስረጃነት ተቀባይነት አግኝተው ለፍርድ ቤት ሲቀርቡ ቀደም ባሉ ከፍተኛ ታዋቂነት ባተረፉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች የፍርድ ሂደቶች ላይ ጭምር ተስተውሏል።[32] የኢትዮጵያ ሕግ ተቀባይነት ስላላቸው እና ውድቅ ስለሚደረጉ ማስረጃዎች፤ እንዲሁም በወንጀል ጉዳዮች የሚቀርቡ ማስረጃዎች ሊያሟሉት ስለሚገባ መስፈርት በተለይ የሚደነግጉ እና ዝርዝር አንቀጾች የሉትም።

በእነዚህ ስድስት የክስ መዝገቦች የተገለጹትን፤ ከላይ የተጠቀሱትን በማሰቃየት የተገኙ የእምነት ቃሎችን እና በፊርማ እንዲያምኑ የተገደዱባቸውን የመወንጀያ ሰነዶች ጨምሮ በቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ላይ አስቸኳይ ምርመራ ሊደረግባቸው ይገባል። የምርመራው ውጤቱም ሰነዶቹ የተገኙት ታሳሪዎቹን በማሰቃየት ወይም በማስፈራራት መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ የቀረቡትን ማስረጃዎች ፍርድ ቤቱ ውድቅ ሊያደርጋቸው ይገባል። በተጨማሪም የማሰቃየት ተግባራትን የሚፈጽሙትን ሰዎች ለይቶ ለማወቅና ተጠያቂ እንዲሆኑም ለማድረግ እንዲህ ያለውን ጥሰት በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በጥንቃቄና በገለልተኛ ወገኖች መጣራት ይኖርባቸዋል። ይሁንና አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባለው መረጃ መሰረት ከዚህ በላይ በተመለከቱት አቅጣጫዎች ምርመራ ለማካሄድ ምንም አይነት ሙከራ አልደረገም።

---

[30] እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳን አንቀጽ 7፣ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ ጠቅላላ አስተያየት 20 ምዕራፍ 12 ይመልከቱ

[31] የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቅጽ 19(5)

[32] አምነስቲ ኢንተርናሽናል 'Justice Under Fire: Trials of opposition leaders, journalists and human rights defenders in Ethiopia' በሚል ሐምሌ 29 ቀን 2011 ያወጣውን መግለጫ ይመልከቱ፡-
http://www.amnesty.org/en/library/info/AFR25/002/2011/en

# ክፍል አራት፡- የፍርድ ሂደቱን በተሟላ መልኩ መከታተል አስፈላጊ ስለመሆኑ

ከላይ የተጠቀሱትን ማብራሪያዎች መሰረት በማድረግ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደሚያምነው በዚህ መግለጫ የተጠቀሱት ግለሰቦች ከመነሻውም የታሰሩት የመንግስት ፖሊሲዎችና አተገባበሮች ላይ ያተኮሩ ትችቶችን በመሰንዘራቸው ሲሆን በጉዳዮቹ ላይም የታየው ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ አትኩሮት በፍርድ ሂደቱ ውጤት ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ከፍ እንዲል አድርጎታል። የፍርድ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ባሉት የእስር ጊዜያት የተፈጸሙባቸውን በሰፊው የተዘገቡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እና በተደጋጋሚ ጊዜያት ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ያለ ምንም ውጤት መቅረታቸው እነዚህ ግለሰቦች ፍትሐዊ የሆነ ዳኝነትን እንደማያገኙና ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለጽና የመደራጀት መብታቸዉን በመጠቀማቸው ብቻ በጥፋተኝነት ሊፈረድባቸው እንደሚችል ተጨማሪ ስጋቶችን ፈጥሯል።

እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እምነት በዚህ መግለጫ የተጠቀሱትን ስድስት የክስ ሂደቶች ዓለም አቀፋዊ ይዘት ካላቸው የፍትሃዊ ዳኝነት መስፈርቶችን አንጻር ያላቸውን ተቀባይነት በቅርብ እና በተሟላ ሁኔታ መከታተል ያስፈልጋል።

ለወትሮው የፍትህ ሂደትን የመከታተል ተግባር ጠንካራ እና ገለልተኛ በሆኑ የሲቪክ ማኅበራት የሚከናወን ነው። ይሁንና በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያሉት የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች የፍርድ ሂደቶችን ለመከታተል በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አይደለም የሚገኙት።[33] በቅርብ ጊዜ በሥራ ላይ የዋለው የሲቪክ ማኅበረሰቡን የሚመለከተው አዋጅ እጅግ አስደንጋጭ የሆነ ጫናን በሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ላይ በማሳረፉ ሥራቸውን የማከናውን አቅማቸውን በጣሙን ውስን አድርጎታል።[34]

የሲቪክ ማኅበራት በአግባቡ ተንቀሳቅሰው መስራት በማይችሉበት ሁኔታ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በአዲስ አበባ ሊሚገኙ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰቡ ተወካዮች የፍርድ ሂደቱን የመከታተሉን ኃላፊነት እንዲወስዱ ጥሪውን ያስተላልፋል። ይህ ጥሪ ካለምንም መነሻ የመነጨ አይደለም። የኢትዮጵያ የውጭ አጋሮች ቀደም ሲል የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ጋዜጠኞች የነበሩበትን የቅንጅት የፍርድ ሂደት ከ2005 እስከ 2007 በነበረው ጊዜ ውስጥ በቅርብ ሆነው ሲከታተሉ ነበር። በእዚህ ክስ ሂደት እስክንድር ነጋ፣ አንዱዓለም አራጌ እና መቶ ሃያ ዘጠኝ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ አባላቶች፣ ጋዜጠኞች እና የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች የተከሰሱበት ነበር።ምንም እንኳን የታዛቢው ግኝት ይፋ ሳይደረግ ቢቀርም፡ የአውሮታ ኅብረት ካውንስል ቋሚ የፍርድ ሂደት ታዛቢ ቀጥሮ ነበር። የአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ኤምባሲ ሰራተኞችም ይህን የፍርድ ሂደት በተዘዋዋሪነት ለመታዘብ ችለዋል። የአሜሪካን ኤምባሲ ሰራተኛም እንደዚሁ ይገኙ ነበር።

በዚህ መግለጫ ትኩረት ለተሰጣቸውን ስድስት የክስ ሂደቶችም በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ልክ ከ2005 እስከ 2007 ባለው የፍርድ ሂደት ላይ የታየውን አይነት ተመሳሳይ አትኩሮት ሊቸራቸው ይገባል። ሁለቱም ተከታታይ የክስ ሂደቶች በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ጋዜጠኞች ላይ በጅምላ የተከፈቱ መሆናቸው ሃሳብን በመግለጽ ነጻነት ላይ ያነጣጠረ ከፍተኛ ዘመቻ መኖሩን ያመለክታሉ። በሁሉም ስድስት የክስ ሂደቶች ላይ ያላሰለሰ ክትትል ማድረግ የዳኝነት አካላቱ በዓለም አቅፍ ደረጃ የተቀመጡትን የፍትሃዊ ዳኝነትን መርሆዎችን አክብረው ሙያዊ ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ እንዲሁም በነጻነት ሃሳብን የመግለጽና የመደራጀት መብቶችን እንዲያስከብሩና ለመወንጀያነት እንዳይዉሉ የመከላከል ግደታቸን እንዲወጡ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

---

[33] አለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ባላቸው አቅም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይንቀሳቀሱ ከፍተኛ ገደብ ተጥሎባቸዋል። የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ተወካዮች በነሐሴ 2011 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ተባረው እንዲወጡ ተደርገዋል።

[34] የበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ (ቁ. 621/2009)

# ማጠቃለያ፡- የቀጠለው የጥቃት ዘመቻ እና ሃሳብን በመግለጽ ነጻነት ላይ እያሳደረ ያለው ከፍተኛ ተጸእኖ

ጠቅለይ ሚኒስትሩ በጥቅምት ወር ለፓርላማው ተጨማሪ እስራቶች እንደሚካሄዱ ያደረጉት ገለጻ የአፈና ዘመቻው መቀጠሉን ያረጋግጣል። በታህሳስ ወር የመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ ቢያንስ መቶ ሰላሳ አምስት ሰዎች በኦሮሚያ ክልል ከተለያዩ ቦታዎች እንደታሰሩ አምነስቲ ኢንተርናሽናል መረጃዎች ደርሰውታል። ከታሳሪዎቹ መካከልም የኦሕኮ እና ኦፌዴን ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ይገኙበታል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የፓርላማ ገለጻ ሌላ የሚያመላክተው ነገር የታወቁ የመድረክ (የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ- የስምንት ዋና ዋና የተቃዋሚ መሪዎች ጥምረት ነው) አመራር አባላትም የመታሰር አደጋ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ነው።

በ2011 ዓ.ም. የተኪያሄዱት እስራትና ክሶች ኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በመግለጽ ነፃነት ላይ ሰፊ የሆነ ጫናን አሳርፈዋልል። እነዚህ ሁኔታዎች ለቀሩት ሌሎች የመንግስት ፖሊሲዎችና አተገባበሮች ላይ ሂስ ለሚሰነዝሩ እና ጥያቄዎችን ለሚያነሱ ሰዎች እራሳቸውን እንዲያቅቡ አለበለዚያ እስራት እንደሚጠብቃቸው ማስፈራሪያ ሆነዋል። ይህ መልዕክት በፈጠረው ስጋትም ቢያንስ ሦስት ጋዜጠኞች እና አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል በ2011 ዓ.ም. መገባደጃ ላይ አገር ጥለው ለመሰደድ በቅተዋል።

በመስከረም ወር ጋዜጠኛ አርጋው አሸኔ ስሙ ዊክሊክስ በተሰኘው የመረጃ መረብ ላይ መጠቀሱን ተከትሎ ከመንግስት የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች የቢሮ ኃላፊዎችና ከፌዴራል ፖሊስ ባለስልጣናት ለምርመራ ከተጠራ በኋላ አገር ጥሎ ለመሰደድ በቅቷል።

በመስከረም እና ጥቅምት ወር የመንግስት ልሳን የሆነው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ በከፋ ሁኔታ የስም ማጥፋት ዘመቻውን ውብሸት ታዬ ከመታሰሩ በፊት ይሰራበት በነበረው በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ በማዞር ቅስቀሳ አካሂዷል። በ2009 ታዋቂና ገለልተኛ የሆነው የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጅ ክፍል የህትመት ሥራቸውን ለማቆም ሲገደዱ የተወሰኑ የጋዜጣው ነባር ዋና አዘጋጆችና ጋዜጠኞች በተመሳሳይ ሁኔታ በዚሁ የመንግስት ልሳን በሆነው ጋዜጣ የማጥላያና የስም ማጥፋት ዘመቻ ሲከፈትባቸ አገር ጥለው ለመሰደድ በቅተዋል። ሁለቱ የአዲስ ነገር ጋዜጠኞች ህዳር 10 ቀን በሌሉበት ክስ ከተመሰረተባቸው ሰዎች መካከል ይገኙበታል። ከመስከረም እስከ ጥቅምት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አትኩሮት ያነጣጠረው አውራምባ ጋዜጣ መስራችና ዋና አዘጋጅ በዳዊት ከበደ ላይ ሲሆን እንዲታሰርም ጥሪ አድርጓል። በህዳር ወር ዳዊት ከበደ በድጋሚ ሊታሰር ስለመሆኑ ከታመነ ምንጭ መረጃ እንደደረሰው አገር ጥሎ ለመሰደድ ተገዷል። ርእዮት አለሙ ትጽፍበት በነበረው የፍትህ ጋዜጣ ላይ አምደኛ የነበረው ጋዜጠኛ አበበ ቶላም በህዳር ወር ከባለስልጣናት በደረሰበት የእስር ማስፈራሪያ የተነሳ ከአገር ለመውጣት ተገዷል። የአንድነት ፓርቲ አባልና የድርጅቱ ልሣን በሆነው ጋዜጣ ላይ ከአንዱዓለም አራጌ ጋር በመሆን ይጽፍ የነበረው ተስፋዬ ደጉም በህዳር ወር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ በሰነዘረው ትችት ሳቢያ ማስፈራሪያ ስለደረሰበት ከአገር ለመሰደድ በቅቷል።

በ2011 ዓ.ም. እየተካሄደ ያለው ሁኔታ የሚጠቁመው የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ውስጥ በቋፍ ላይ የሚገኘውን ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት ቁርጦ መነሳቱን ነው። የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ግለሰቦችና ህትመቶች፣ የተለያዩ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን የሚወክሉ ግለሰቦችን ወይም በአገሪቷ የፖለቲካ ሂደት ላይ ገለልተኛ የሆኑ አስተያየቶችን የሚሰጡ ሰዎች ለጥቃት የማይጋለጡበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተሚጧል።

# የመፍትሄ ሃሳቦች

## ለኢትዮጵያ መንግስት

### አምነስቲ ኢንተርናሽናል ለኢትዮጵያ መንግስት የሚያቀርበው ጥሪ፡-

### ፍትሃዊ ዳኝነትን ስለማግኘት

- በኢትዮጵያ ውስጥ ክስ የተመሰረተባቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች የፍርድ ሂደት ስለ ፍትሃዊ ዳኝነት የተቀመጡትን ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶች ባሟላ መልኩ እንዲከናወኑ  አስፈላጊ የሆኑትን እርማጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ፣
- በስድስቱም የክስ መዝገቦች በማስረጃነት ከቀረቡት ነገሮች መካከል የእምነት ቃሎችንና በፊርማ እንዲረጋገጡ ተደርገው የቀረቡ የመወንጀያ ሰነዶችን ጭምር ታሳሪዎችን በአስጨናቂ ሁኔታች  ስር አድርጎ በኃይል የተገኙ ስለሆኑ ባፋጣኝ ጥንቃቄ በተሞላውና በገለልተኛ አካል ማጣራት እንዲካሄድባቸው፣ የማጣራቱም ውጤት ማስረጃዎቹ ታሳሪዎችን በማሰቃየትና በማስጨነቅ የተሰባሰቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ከሆነ እንዲህ ያሉት ማስረጃዎች በፍርድ ቤቱ ውድቅ እንዲደረጉ፣
- በሰላማዊ መንገድ ሃሳባቸን በነፃነት የመግለጽ፣ የመደራጀት እና የመሰብሰብ መብታቸውን ተጠቅመው በመንቀሳቀሳቸው ብቻ ለእስር ተዳርገው በአሁኑ ሰዓት ክስ የተመሰረተባቸውን የተቃዋሚ ፓርት አባላትና ጋዜጠኞች የፍርድ ሂደት ባፋጣኝ እንዲያቆም እና በዚህ ምክንያት የታሰሩ ሰዎችን በጠቅላላ ባፋጣኝና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ፣
- የዓለም አቀፉ የዲፕሎማሲ ማኅበረሰብም የፍርድ ሂደቱን በተሟላ መልኩ እንዲከታተሉ እንዲፈቅድ። እንዲሁም የፍርድ ሂደቱን በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፤ ችሎቱ የሚካሄድበትን ሥፍራ እና ሰዓት በተገቢው ጊዜ ውስጥ ለጠቅላላው ማኅበረሰብ መገለጻቸውን እንዲያረጋግጥ፤

### ማሰቃየት እና ሌሎች በደሎችን በተመለከት

- በዚህ መግለጫ በተጠቀሱት ስድስት የክስ መዝገቦች ውስጥ ያሉ ተከሳሾች ባቀረቡት አቤቱታ የደረሰባቸውን የማሰቃየትና ሌሎች በደሎች ሳይዘገይ፣ ተገቢ ጥንቃቄ በተሞላበት፣ አጥጋቢ በሆን መልኩ እና በገለልተኛ አካላት እንዲጣሩ እና ድርጊቶቹ ለመፈጸማቸው በበቂ ሁኔታ በማስረጃዎች ከተረጋገጠ ጥሰት ፈጻሚዎቹ ላይ ክስ እንዲቀርብና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው ፍትሐዊ የፍርድ ሂደት ከሞት ፍርድ መለስ ተገቢውን ቅጣት ማግኘታቸውን እንዲያረጋግጥ

### ሕገ-ወጥ እስራት እና መሰወር

- የፍትሕ ሚኒስቴር እና ሌሎች የሕግ አስፈጻሚ አካላት በ2011 ዓ.ም. ስለ ታሰሩት የኦሕኮ እና ኦፌዴን ፓርቲ አባላትና ከጅማ፣ ከሃሮማያ እና ከነቀምት የተያዙ ተማሪዎችን እና ሌሎች በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የታሰሩ ግለሰቦችን ጨምሮ ስለ

ሁሉም ታሳሪዎች የተሟላ ዝርዝር መረጃዎችን፤ ስሞችን፣ አሁን ታስረው የሚገኙበትን ስፍራ እና የታሰሩበትን ሁኔታ የሚያካትት መስጠታቸውን እንዲያረጋግጥ፣

- ክስ ሳይመሰረትባቸው እስከ አሁን በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎች የታሰሩበት ሕጋዊ አግባብ እንዲጣራ መጠየቅ እንዲችሉ ባፋጣኝ የፍትህ አካላት ዘንድ መቅረባቸውን እንዲያረጋግጥ፣
- ሁሉም ታሳሪዎች በህግ በተመለከቱ የወንጀል አድራጎት ብቻ ክስ እንዲመሰረትባቸው ወይም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ባፋጣኝ እንዲለቀቁ እንዲያደርግ፣
- አሁን በእስር ላይ የሚገኙ ታሳሪዎችን በተመለከተ ያሉበትን ሁኔታና የታሰሩበትን ስፍራ ለቤተሰቦቻቸው እንዲያሳውቅ እና እንዲጎበኙዋቸው እንዲፈቀድ፣
- ለሁሉም ታሳሪዎች ባፋጣኝ እና በተሟላ መልኩ የሕግ ተወካዮችን እንዲያገኙ መደረጉን እንዲያረጋግጥ፣
- የታሰሩ ሰዎች በሕግ ባልታወቁ የሥውር ማጎሪያ ስፍራዎች እንዲቆዩ እንደማይደረግ እንዲያረጋግጥ። በእነዚህ ሥፍራዎች ታስረው የሚገኙ ሰዎችን ባፋጣኝ በሕግ ወደታወቁ እስር ቤቶች እንዲዘዋዋሩ፣

## የእስረኞች አያያዝን በተመለከተ

- ማንም ሰው፤ በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎችን ጨምሮ ስቃይ ወይም ሌሎች አይነት ጭካኔ የተሞላቸው፣ ኢ-ሰብዓዊ የሆኑ ወይም ለሰው ልጅ ከሚገባው ክብር ውጪ የሆኑ ሊፈጸሙበት እንደማይገባ በይፋ እንዲገለጽና ይኸውም በፖሊስ እና በሌሎች ሕግ አስፈጻሚ አካላት መከበሩ እንዲረጋገጥ፣
- እስር ቤቶች እና ሌሎች የማቆያ ስፍራዎች እንዲሁም እስረኞች (እንዲሁም በሌሎች ሁኔታዎች የመንቀሳቀስ ነፃነታቸውን የተነፈጉ) በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ እስር ቤቶችንና ማቆያዎችን እንዳይጎበኝ በተከለከለው እንደ አለም ዓቀፍ ቀይ መስቀል ባሉ መንግሥታዊ ባልሆኑ ገለልተኛ አካላት ፤የሚጎበኙበትን ሁኔታ ማመቻቸትና እነዚህ አካላት በገለልተኝነት የእስር ቤቶቹን ሁኔታ እንዲያጠኑና ክትትልም እንዲያደርጉ እንዲፈቀድ፤ እንዲሁም የታሳሪዎቹን ሁኔታና አያያዝ አስመልክቶ የሚያቀርቡት ሃሳብ ከግምት ውስጥ እንዲገባ።

## ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ

**ለተባበሩት መንግስታት፣ ለአውሮፓ ኅብረት፣ ለአፍሪካ ኅብረት እንዲሁም ሌሎች ከኢትዮጵያ ጋር ቅርብ የሆነ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ያላቸው እና በእርዳታ እና በፖለቲካዊ ግንኙነታቸው ውስጥም የሰብዓዊ መብቶች መከበርን ለማካተት ቃል ለገቡና ይህንንም በፖሊሲ ደረጃ ላስቀመጡት መንግስታትና አካላት  አምነስቲ ኢንተርናሽናል፡-**

በመካሄድ ላይ ያለውን ከሽብርተኝነት ጋር የተያያዘውን የፍርድ ሂደት እና በ2011 ዓ.ም. ታስረው ክሳቸው በመታየት ላይ ያለውን የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት የፍርድ ሂደት አዲስ አበባ በሚገኙ ተወካዮቻቸው አማካይነት በተሟላ መልኩ እንዲከታተሉ፤ በክትትሉ የሚገኙ መረጃዎችን ለሕዝብ ይፋ እንዲያደርጉ እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያካፍሉ ጥሪ ያቀርባል።

# ተጨማሪ መግለጫ፡- በስድስት ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ክሶች እና ተከሳሾች

## በተሻለ በካሺ እና ሌሎች የክስ መዝገብ የተከሰሱ

1. ተሻለ በካስሂ አያና
2. ትርፌሳ መገርሳ ሁንዴ
3. አለማየሁ ጉናሶ ጪምሳ
4. ሙላቱ አብዲሳ ጎባና
5. ልጅዓለም ታደሰ ጉዲና
6. ሃሰን ሙሃመድ አሚን
7. አዱኛ ቤኛ
8. ሚሊኬሳ ዋቅጂራ ገመዳ
9. ሳምሶን አለሙ ቂጤሳ
10. ገመቹ አሚሶ ገልገሎ
11. ሁስማን ሁማር ተሶጊሎ
12. ጃርሶ ቦሩ ራሮ
13. ኢስማኤል ከሊፋ ሙዚን
14. ከፋለ ፈጠነ ገበየሁ
15. ጉቱ ሙሊሳ ገደፋ
16. ሁሴን በርሶ ጎዳና
17. ቶሎሳ በቾ
18. ካኑ ጉኖስ ደምሴ
19. ግዛቸው አብዲሳ ባይሳ
20. ኢታና ሰንበቶ ቱቾ
21. ለሜሣ ደሲሳ ገነቴ
22. አበራ ቢቂላ ቶሎሳ
23. ቱኪ ቲቢሶ
24. በላይ ኮርሚ ባይሳ
25. ሃሰን አማን ሲጋ
26. መዝገቡ ደበሌ ዋቅጅራ
27. አሰፋው አንገሱ በንቲ
28. ቦንቱ ወዳይ ቡላ (ሴት)
29. በሺር ዳዲ ፉፋ
30. አለማየሁ ቶሎሳ ሊበን
31. ሃዊ ጎንፋ ደበላ (ሴት)
32. ታደሰ ገላሊቻ

33. ተፈሪ ቀነኒሳ ገመቹ
34. ቡልቻ ሶርሳ
35. ሞሃመድ ሰሊሆ ዋቆ
36. ሶርሳ ደበልላ ገላሊቻ
37. ተሻለ ኢዶሳ ዲርባ
38. ኢርፓ ዱበ ዲካሞ
39. ሙክታር ኡስማን
40. ኡማር ባሳ
41. ሞሃመድ ሁሴን
42. ቻሊ ቶሎሳ ኒካ
43. ድሪባ ነጋሳ ሙለታ
44. መንገስሃ ቶሎሳ ደሲይ
45. አመንቲ ሶሎሞን በቀለ
46. ኑሬ ሃጂ ከማል
47. ወጋየሁ
48. ታደሰ ሞቲ ቱራ
49. አብዱራዛቅ አባቢያ
50. መንግስቱ ወርዶፋ
51. ኤፍሬም ገለታ
52. ሞሃመድ ቱኩይ
53. ቶሎሳ በዳዳ
54. መንግስቱ ግርማ
55. ራሺድ ጃሚል
56. ታከለ አብደታ
57. ካሊል ጃሚል
58. ምለሡ ቻላ
59. ሁሰን አብደላ
60. ዋሲ ጋዲሳ
61. ሶሎሞን ተመስጌን በላይ
62. ጌታቸው ኢዶሳ
63. ታሪኩ ደቢሳ
64. ዋጋሪ ላጪሳ
65. ኤርፓሳ ድሪሳ
66. ጫሉማ ሊከሳ
67. ጉርሜሳ ቱርፋ
68. ጪምደሳ ሚንታሳ ጉታታ
69. ዳዊት አብዲሳ

## በጌትነት ገመቹ ገመታ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ

1. ጌትነት ገመቹ ጉምታ
2. ተካልኝ አበራ ገመዳ
3. ሚተኩ ጌታቸው እጀታ
4. አቦሳ አለሙ ፎግሃ ዳኖ
5. ጌቱ አሰፋ ኢሪሳ
6. ዶዶላ ቡና ፊንቁሌ
7. ራቢራ አደሪ ቡዙ
8. ሙሃዲን አባቡልጉ አባገሮ
9. ከሃሊድ ሞሃመድ አብደላህ
10. ተስፉ ሞቶራ ዋየሳ
11. መገርሣ ኩማ ዲሪርሳ
12. ደሚሰ ደበሳ ኢንሳ
13. ዋጋሪ ድሪብሳ ዊቱ
14. ደሳለኝ ደቦል ሆራ
15. ጌታቸው ቡሩ ጉርመሳ
16. ቻሌ አብዲሳ ቡልጉ
17. ሃምዛ አብዱ ኢብራሂም
18. ኮ/ል ፈቃዱ ረጋሳ ጆሉ
19. ደርባቸው አመንቴ ቡሊ
20. ለቺሳ ኢዶሳ ድሪባ

## በበቀለ ገርባ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ

1. በቀለ ገርባ ዳኮ
2. ኦልባና ለሊሳ ኦልጂራ
3. ወልበቃ ለሚ ደደፊ
4. አደም ቡሳ ካቤቶ
5. ሃዋ ዋቆ ቦሩ
6. ሞሃመድ መሉ ሰሪ
7. ደረጀ ከተማ ሞቱማ
8. አድዲሱ ሞከሬ ገብረጊኦርጌስ
9. ገልገሎ ጉፋ አባዮ

## በኤልያስ ክፍሌ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ

1. ኤልያስ ክፍሌ
2. ዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር

3. ዉብሸት ታዮ አበበ
4. ሂሩት ክፍሌ ወልደየስ
5. እርዮት አለሙ ዘበቦ

## በአብዲወሊ ሞሀመድ ኢስማኤል እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ

1. አብዲወሊ ሞሃመድ ኢስማኤል
2. ከሊፋ አሊ ዳሂር
3. ማርቲን ሺብዮ
4. ጆሃን ፐርሶን

## በአንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች መዝገብ የተከሰሱ

1. አንዱዓለም አራጎ ዋሴ
2. ናትናኤል መኮንን ገብረኪዳን
3. ዮሃንስ ተረፈ ከበደ
4. የሺዋላ ይሁንዓለም
5. ክንፈሚካኤል ደበበ በረደድ
6. ምትኩ ዳምጤ ወራኩ
7. እስክንድር ነጋ ፋንታ
8. አንዱዓለም አያሌው ገላው
9. አንዳርጋቸው ጽጌ
10. ብርሃኑ ነጋ ቦንጋር (ዶ/ር)
11. ውቤ ሮባ
12. ኤፍሬም ማዴቦ
13. መስፍን አማን
14. ዘለሌ ጸጋስላሴ
15. ፋሲል የኔዓለም
16. አበበ በለው
17. አበበ ገላው
18. ነአምን ዘለቀ
19. ኤልያስ ሞላ
20. ደሳለኝ አራጌ ዋሴ
21. ኮ/ል አለበል አማረ
22. አባንግ ሜቶ
23. መስፍን ነጋሽ
24. አብይ ተክለማርያም